# የዉሃ ጥምቀት ፤ የጌታ እራት እና እግር ማጠብ

በኢ. ፍራንክ

## መግቢያ

የውሃ ጥምቀት እና የጌታ እራት በአብዛኞቹ የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት የሚተገበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓቶች ናቸው፣ ምንም እንኳን አተገባበራቸው በተለያዩ መንገዶች ቢሆንም:: ነገር ግን የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስርአቱን ስተፈጽምበት የነበረዉ የመጀመሪያው መንገድ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሂደት ውስጥ ጠፍቷል:: ለዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እና ተሐድሶ አራማጆች አንድን ቃል በመጠቀም ሲከራከሩና ሲጣሉ ቆይተዋል:: ነገር ግን ስምምነት ላይ መድረስ አልቻሉም፣ እና ልዩነቶቹም እንዳሉ ቀርተዋል:: መመለስ ወደ አለብን ወደ መጀመሪያቱ ቤተ ክርስቲያን ልምምዶች ጋር አይጣጣሙም::

ስለ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች "በሐዋርያት ትምህርት ጸንተው ቆዩ..." (የሐዋርያት ሥራ 2:42) ብለን እናነባለን:: ሐዋርያት በጌታ እንደተጠሩና ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የተያያዙ ምስጢራትን ማግኘት እንደሚችሉ ተገንዝበዋል:: ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆይቷል " እስከዓረገበት ቀን ድረስ ለመረጣቸዉ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሰጣቸው ትእዛዝ ነዉ::ከሕማማቱ በኋላ እራሱ ቀርቦ ሕያዉ መሆኑን ለእነዚሁ በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸዉ አርባ ቀንም እያታያቸዉ ስለእግዚአብሔር መንግስት ነገራቸዉ" (የሐዋርያት ሥራ 1:2-3):: ከመንግሥቱ ጋር የተያያዙትን ነገሮች ሁሉ እንደተናገረ ማወቃችን ደስ ይለናል::ትእዛዙን የሰጠው እርሱ ነበር:: በዓለ ሃምሳ በተባለዉም ቀን መንፈሱን በእነርሱ ላይ ላከ እና ምን መደረግ እንዳለበት እና እንዴት በእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ መሠረት መከናወን እንዳለበት በትክክል ገለጠ::

ጳውሎስ ከመጀመሪያው ጀምሮ ከእነርሱ ጋር አልነበረም:: እርሱ በመጀመሪያ የእራሱ "የነገረ መለኮት ጥናት" ነበረዉ፣ ነገር ግን ከተለወጠ በኋላ እንደሌሎቹ ሐዋርያት ተመሳሳይ ወንጌልና ተመሳሳይ ትምህርቶችን ሰበከ:: በቀጥታ በራእይ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ የሰበከው ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር የሚስማማ መሆኑን በማነጻጸር ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ:: ካአለበለዚያ፤ በከንቱ ሮጦ እንዳይሆን ፈራ (ገላ. 2:1-2)::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እና መልእክቶች በትምህርቶች ውስጥ ፍጹም ስምምነትን ይመሰክራሉ፣ እንዲሁም ከአራቱ ወንጌሎች እና ከብሉይ ኪዳን ጋር። ስለዚህ፣ በሐዋርያት የተተወልን ሁሉ ንጹህ ትምህርት እና ልምምድ ነው። እዚህ የጴጥሮስን ወይም የጳውሎስን አስተያየት አንመለከትም፣ ነገር ግን በቀጥታ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃልና ዕቅድ እንመለከታለን። ዛሬም ቢሆን ያ ሁሉ ነገር መረጋገጥ ያለበት ብቸኛው ጠቃሚ መለኪያ ነው።

አንድ ጊዜ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን “ይህን ሁሉ ተረድታችኋልን? እነርሱም፣ አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ አሉት። እርሱም፣ ስለዚህ የመንግሥተ ሰማያት ደቀመዝሙር የሆነ ጻፊ ሁሉ ከመዝገቡ አዲሱንና አሮጌዉን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል አላቸዉ ” (ማቴ. 13:51-52) ። ጌታ በሁሉም ጊዜ በመንግሥቱ ውስጥ ለተወሰኑ ዓላማዎች የጠራቸውን ሰዎች ይጠቀም ነበር። እነርሱ በሰማያዊው ትምህርት ቤት እንደተማሩት የነገረ መለኮት እውቀትን አላቀረቡም። የዚህ ዓለም አዋቂዎች የተደበቀባቸውን እንደሰማያዊ ጥበብ ተናገሩ። የእርሱ መልእክተኞች ሁልጊዜ ቃሉንም መንፈሱንም ተቀብለዋል። ስለዚህ የፈቃዱ ግልጽነት እና መገለጥ ነበራቸው እና ትክክለኛውን አተገባበር ያውቁ ነበር። ለዚህ የማይሳሳት ምልክት ስብከታቸው እና ልምምዳቸው ከመጻህፍ ቅዱስ ሁሉም ጥቅሶች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ መሆኑ ነው። ጌታችን እና ሐዋርያት በዚያን ጊዜ የነበራቸው ብሉይ ኪዳን ብቻ ነበር። ደጋግመው ወደ እሱ ይጠቅሱ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከብሉይ ኪዳን 845 ጥቅሶችን እናገኛለን።

የዛሬ ወንጌል ሰባኪዎች በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። በእግዚአብሔር መንግሥት የሚያገለግል ሁሉ የሚያስተምረውንና የሚተገብረውን ከጳውሎስና ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር ለማነጻጸር ድፍረት ሊኖረው ይገባል። ከመጀመሪያው አዋጅና አተገባበር ጋር የማይስማማ ከሆነ፣የሆነ ቦታ የሆነ ስህተት አለ። ጳውሎስ በከንቱ እያገለገለ እንዳልነበር ትምህርቶቹን ከሐዋርያት ትምህርቶች ጋር ማነጻጸር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ፣ ታዲያ ከእኛ መካከል ማንም ይህን ማድረግ እንዴት ሊዘነጋ ይችላል?ከመጀመሪያዉ ጋር የማይወዳደር ከእግዚአብሔር ከመጣው ሁሉ ጋር ማስመሰል እና ማጭበርበር እናገኛለን።

ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በላከው መልእክት ላይ "...ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸዉ አዉቃለሁ" (ራእይ 2:2) የሚለውን እናነባለን። ይህ ፍርድ ሊሆን የቻለው አድማጮች የተሰበከላቸውን ከመጀመሪያው ሐዋርያዊ ትምህርት ጋር በማነጻጸር ነበር። እነዚያ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ ክርስቲያኖች እነዚህ ሰዎች ሐዋርያት ነን ብለው ብቻ እንደሚናገሩ ነገር ግን በእርግጥ ውሸታሞች እንደሆኑ አስተዋሉ ምክንያቱም ቀደምት ሐዋርያት እንዳደረጉት ንጹሕ የሆነውን መለኮታዊ መልእክት አልሰበኩም።

በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስለ ውኃ ጥምቀት፣ ስለ ጌታ እራት እና ስለ ሌሎች ትምህርቶች ምንም ዓይነት እርግጠኛ አለመሆን አልነበረም። ጌታ እነዚህ ነገሮች እንዴት መወሰድ እንዳለባቸው ግልጽ ምክር ሰጥቶ ነበር። ስለዚህ ስለሚልካቸዉ ሰዎች እንዲህ ሊል ችሏል፣ "እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል" (ሉቃስ 10:16)። ጥምቀት እና የጌታ እራት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዴት እንደተገለጹ ማሳየት አለብን። ከጌታ እራት ጋር ፤ የእግር ማጠብም የተያያዘ ነው ይኸንም በአጭሩ በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን እናያለን።

እ.ኤ.አ ታህሳስ 1986

## ጥምቀት

በመጀመሪያ ስለ ውኃ ጥምቀት በአጭሩ እንመለከታለን። ጌታ እንድናጠምቅ አዘዘን፣ ስለዚህም ጥምቀት በክርስቲያናዊ ቤተ እምነቶች ውስጥ እየተፈጸመ ነው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በእርግጥ፣ ከመጀመሪያው ትምህርትና አሠራር መለየትን ያሳያል። በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት ጥምቀት ብቻ ነበር። ዛሬ ግን ጥምቀት የሚፈጸምባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ።

በኤፌሶን ለነበሩት አማኞች የተነገረው ቃል ዛሬም በማንኛውም ቦታ ላለ ለማንኛውም አማኝ ትክክለ ነው፣ "አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት፣ አንድ ጥምቀት" (ኤፌ. 4:5) ። በእርግጥ፣ አንድ ጌታ ብቻ ነው ያለው፣ እርሱም እግዚአብሔር ነው፣ አንድ እውነተኛ እምነት ብቻ ነው ያለው፣ እርሱም የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ነው፣ አንድ ጥምቀት ብቻ ነው ያለው — እርሱም በሐዋርያት የተፈጸመው ነው።

በዚህ ማብራሪያ ውስጥ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንፈልጋለን፡- ጥምቀት ምን ማለት ነው? ለምን ይፈጸማል? ማን ሊጠመቅ ይችላል? እና በመጨረሻም፡- በተግባር እንዴት ይፈጸማል?

### አስፈላጊነቱ

በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ፣ መጥምቁ ዮሐንስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" (ማቴ. 3:2) እያለ ሰበከ። ጌታችን ዮሐንስንና አገልግሎቱን ደጋግሞ ጠቅሷል። በሉቃስ 7:29-30 ላይ እንዲህ ይላል፣ "የሰሙትም ሕዝብ ሁሉ ቀራጮችም እንኳ ሳይቀሩ በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው እግዚአብሔርን አጸደቁ። ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች ግን በእርሱ ስለ አልተጠመቁ  የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ።" ኢየሱስ ክርስቶስም እንኳ "ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናልና አሁንስ ፍቀድልኝ" (ማቴ. 3:15) በማለት በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ ሊጠመቅ ሄደ።

ጴጥሮስ በብዓለ ሃምሳ ቀን በመጀመሪያው ስብከቱ ላይ፣ ለጠያቂው ሕዝብ እንዲህ አላቸው፣ "ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" (ሐዋ. 2:38)። ጥምቀት

የግለሰብ ምርጫ አይደለም፣ ይልቁንም የአማኙን ታዛዥነት ለማሳየት አስፈላጊ ነው። የቤዛነቱን ስራ እዉቅና የሚሰጥ እና ክርስቶስን በእምነት የሚቀበልና በዚህም ጽድቅን የሚያገኝ ሁሉ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ መሆን አለበት።

ሐዋርያው ጴጥሮስ የጥምቀትን አስፈላጊነት በኖኅ መርከብ ምሳሌ ያሳያል ፣ በ1ጴጥ 3:20-21 ላይ እንደሚገኘው "ጥቂቶቹ ማለት ስምንት ነፍስ በዉኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ ፤የእግዚአብሕር ትእግስት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ወኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ አሁን ያድነናል ፤ የሰዉነት እድፍ ማስወገድ አይድለም ... " ጎርፉ መርከቡ ዉስጥ ከነበሩት በቀር ሁሉንም አጠፋ። የኖኅን ስብከት የሰሙ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። ጥቂቶች ብቻ የዚያን ነቢይ መልእክት አምነው ከእርሱ ጋር ገቡ።

ጴጥሮስ የመርከብን ምሳሌ ከአማኞች ጥምቀት ጋር ለምን እንዳገናኘ ልንጠይቅ እንችላለን። አንድ ሰው በእውነት ካመነ፣ ጌታ የተናገረውን ያደርጋል እና ወደ ክርስቶስ ይጠመቃል ፤እርሱ የእኛ መርከብ ነው፣ ብቸኛው የመጠጊያና የደህንነት ቦታ። በእርሱ ብቻ፣ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ እናመልጣለን። መዳን ወደ እኛ የሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው። አማኞችም ከዚያ ለቃሉ በመታዘዝ እርምጃ ይወስዳሉ እና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጠመቃሉ። ማንም ሰው መለኮታዊው ሥርዓቱን ካልተከተለ፣ እርሱ ወይም እርሷ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ አለማመንና አለመታዘዝን በግልጽ ያሳያሉ፣ እናም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አንድ ሰው የደህንነት መርከብ ወደ ሆነዉ ወደ ክርስቶስ አይመጣም። ታላቁ ጎርፍ ሲመጣ፣ ክርስቲያን ነን የሚሉ ብዙዎች ራሳቸውን ከውጭ ሆነው ያገኙታል እና ይጠፋሉ።

በእርግጥ ሰዎች ከጎርፉ በፊት "ለምን ወደ መርከብ መግባት አለብን? ውኃው የት አለ? እግዚአብሔርን እናምናለን፤ ያ በቂ መሆን አለበት። ሁሉም ነገር እንደነበረው ይቀጥላል። ይህን ሰባኪ መስማት አያስፈልገንም" ብለው ጠይቀው ይሆናል። ኖኅን ከጌታ ቀጥተኛ ተልእኮ ያለው ነቢይ እንደሆነ አላወቁትም። የጊዜ ቆጠራዉ ያኔ ጀምሮ ነበር፣ አሁንም ጀምሯአለ። ምንም እንኳ ሁሉም ማስጠንቀቂያዎች ቢደረጉም፣ ሰዎች የራሳቸውን መንገድ ሄዱ እና አልሰሙም። በድንገት፣ ቀኑ ደረሰ፣ የተተነበየው ጥፋት

በሰው ዘር ላይ ወረደ:: በድንገት፣ በሩ ተዘጋ:: ከውጭ የነበሩት ጠፉ:: አሁንም ቢሆን፣ ሁሉም ነገር እንደነበረው የቀጠለ ይመስላል (2 ጴጥ. 3:4)፣ ነገር ግን በቅርብ ጊዜ ውስጥ፣ ክርስቶስ ሲመለስ፣ ልዩነቱ ይታወቃል:: የእግዚአብሔር ሰዓት በድንገት ይመጣል:: የጸጋው ዘመን ያበቃል፣ በሩም ይዘጋል:: በውስጥ ያሉት ፤ ለዘላለም ደህና ይሆናሉ::

ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በጥንት ዘመን የተባለውን ብቻ መድገም እንችላለን፣ "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፣ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣ በምድረ በዳ በፈተና ቀን ፤በዓመጽ እንዳደረጋችሁት፤ ልባችሁን አታደንድኑ " (ዕብ. 3:7-8) :: እስከ መጨረሻው ድረስ ቃል ኪዳኑ ትክክል ነው፣ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" (ማር. 16:16) :: ለመታዘዝ ፈቃደኛ የሆነ ማነው? እውነተኛ እምነት የሚታየው ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ነው:: የሚያስፈለጉ ስራዎች የሌለዉ እምነት በራሱ የሞተና ከንቱ ነው:: በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ እስካሁን አንድም ሰው ያላዳነ ሃይማኖታዊ ኑዛዜ ብቻ ነው:: ሁሉም የክርስቲያን ትምህርቶች ከንቱ ናቸው:: የክርስቲያን ትምህርቶቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ከግለሰቦቹ ልምምዶች ጋር የተያያዙ መሆን አለባቸው:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በቃሉ እና ወደ ሕይወት በሚያመጣው መንፈስ ነው:: ከእርሱ የሚመጣው ብቻ ወደ እርሱ ይመልሰናል:: ስለዚህ፣ ለውኃ ጥምቀት መታዘዝ 'ሊሆን ይችላል' ሳይሆን ለእያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ 'ግድ' ነው::

### ትርጉሙ

ጥምቀት በቀላሉ አንድ ሰው እራሱን ከክርስቶስ ሞት፣ ቀብር እና ትንሳኤ ጋር አንድ ይሆን ዘንድ የሚያደርገዉ ተግባር ነው:: በጥምቀት የኃጢአት ስርየት የለም:: ለመጠመቅ የሚጠይቀው ሰው ይልቁንም በቀራኒዮ መስቀል ላይ በፈሰሰው ደም የኃጢአት ስርየትን እንደተቀበለ ያሳያል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "...ይህም ወኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ አሁን ያድነናል ፤ የሰዉነት እድፍ ማስወገድ አይድለም ፤ ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነዉ እንጅ ፤ ይኸም በእየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነዉ ፤" (1ጴጥ. 3:21) :: የሚጠመቀው ሰው ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ በመገንዘብ ራሱን ከክርስቶስ ጋር አንድ ያደርጋል::

ጥምቀት አንድ አማኝ በጌታውና በአዳኙ ላይ የግል እምነቱን ከመሰከረ በኋላ የሚፈጽመው የመታዘዝ ተግባር ነው:: ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃ እንደገቡ እናነባለን:: በዚህ መንገድ ዛሬም ቢሆን በሁሉም መጽሐፍ ቅዱስን በሚያምኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ይከናወናል:: ሁለቱም፣ የሚያጠምቁትና የሚጠመቁት እስከ ወገባቸው ድረስ ወደ ውሃ ይገባሉ:: ከማጥመቁ በፊት፣ የሚያጠምቀው ሰው እንዲህ ያለ ነገር ይናገራል፣ “ወንድም እገሌ፣ እህት እገሌ፣ በእምነታችሁ ምስክርነት መሰረት እንደእግዚአብሔር ቃል በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠምቃችኋለሁ::” ጥምቀቱ ራሱ ከቀብር ጋር ይነጻጸራል:: ስለዚህ ሰውየው ወደ ውኃው ወደ ኋላ ይተኛል እና ሙሉ በሙሉ ይሰምጣል፣ ከዚያም እንደገና ይነሳል:: ከውኃ መውጣት የሚያሳየዉ የተጠመቀዉ ሰዉ ከክርስቶስ ጋር ለአዲስ ሕይወት መነሳቱን ነው:: ነገር ግን አዲሱ ሕይወት፣ በእርግጥ በጥምቀት አይመጣም ፤ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ በኩል በአዲስ ዉልደት ነው:: በማንኛውም ሁኔታ፣ ትንሽ ውሃ በግንባሩ ላይ ስለተረጨ ወይም ስለፈሰሰ፣ “ጥምቀት” ተብሎ ሊጠራ አይገባም፣ ምክንያቱም ጥምቀት ስላልሆነ::

ሐዋርያው በቆላ. 2:12 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ “... በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፣ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሳዉ በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ ::” መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሕፃን በመርጨት ወይም በማፍሰስ እንደገና እንደሚወለድ አያስተምርም — በተቃራኒው፡ ግልጽ ትምህርቱ ሰዎች በመጀመሪያ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መስማት፣ ቃሉን እንደ ዘር ወደ ነፍሳቸው መቀበል፣ እና በእግዚአብሔር መንፈስ አዲስ ሕይወት ማግኘት አለባቸው:: ከዚያ በኋላ ብቻ መጠመቅ አለባቸው:: የውኃ መጥመቅ እንደዚሁ በራሱ መንፈስ ቅዱስን መቀበልን አያመለክትም:: በመንፈስ መጠመቅ የተለየ ልምምድ ነው:: በመንፈስ መጠምቅ ለውሃ ጥምቀት ለታዘዘው አማኝ የእግዚአብሔር መልስ ነው:: በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ ሰውየው የእግዚአብሔር እንደሆነ ማረጋገጫ ይቀበላል::

በሮሜ 6:4-5 ላይ፣ ሐዋርያው ጥምቀትን በሚከተሉት ቃላት ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል፣ “እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፤ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን:: ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሳኤዉን በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ

ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤" ተመሳሳይ ሐሳብ በገላትያ ሰዎች መልእክቱ ምዕራፍ 3:26-27 ላይ ተገልጿል፣ "ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና። ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።" ከውኃው ውስጥ እርጥብ ሆኖ ለመውጣት ወደ ውኃው የሚገባ ደረቅ ኃጢአተኛ አይደለም፣ አይደለም፣ እኛ የምንናገረው ከእግዚአብሔር ጸጋ ያገኙ፣ ከእርሱ ጋር የታረቁ፣ ኃጢአታቸው እንደተሰረየላቸው ማረጋገጫ ያገኙ፣ እግዚአብሔር እንደተቀበላቸው እርግጠኛ የሆኑ ሰዎችን ነው።

## ቅድመ ሁኔታው

አንድ ሰው ለመጠመቅ መሠረታዊው ቅድመ ሁኔታ በአዳኙ ላይ ያለው የግል እምነቱ ነው። ጌታ ወደ ሰማይ ከማዕረጉ በፊት፣ በጣም ግልጽ የሆነ ትእዛዝ ሰጠ፣ "እንዲህም አላቸው፡- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል'" (ማር. 16:15-16)። እንደምናየው፣ መጀመሪያ የሚመጣው የወንጌል ስብከት ነው እንጂ ሃይማኖታዊ ድርጊት አይደለም።

በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለታረቅንበት በመስበክ ሰዎች የእግዚአብሔርን የማዳን አቅርቦት እንዲቀበሉ ይደረጋሉ። እንደተጻፈው፣ "እምነት ከመስማት ነው፣ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው" (ሮሜ 10:17)። በመንፈስ ቅዱስ በአድማጮች ልብ ውስጥ የሚሠራ እንዲህ ያለው እምነት መጀመሪያ መምጣት አለበት። ወደ እግዚአብሔር ውስጣዊ "አዎ" እና የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ጸጋ በልባችን መቀበል መኖር አለበት። አንድ ሰው መጀመሪያ የመዳን ልምምዱ ሊኖረው ይገባል፣ በዚህም አማኝ ይሆናል። እንደ ሮሜ 8:16 " የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።" ይህ በእምነት በቤዛነት የተጠናቀቀውን ሥራ በማመን በእግዚአብሔር ፊት የጸደቀ ሁሉ የሚያገኘው ማረጋገጫ ነው።

ከዚህ በኋላ በቀላሉ የሚመጣው ቀጣዩ እርምጃ ጥምቀት ነው። በሐዋርያት ሥራ 2:41 ላይ "ቃሉንም በደስታ የተቀበሉ ተጠመቁ" ብለን እናነባለን። ይህ የሆነው ጴጥሮስ በብዓለ ኃምሳ ቀን የመጀመሪያውን ስብከት ከሰበከ በኋላ ነው። አስደናቂ ውጤት ነበር። ወደ 3,000 የሚጠጉ ሰዎች መለኮታዊውን መልእክት ተቀበሉ፣ የተሰበከላቸውን የእግዚአብሔር ቃል አመኑ እና ወዲያውኑ ተጠመቁ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ስርዓት ከክርስቶስ በኋላ እስከ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ነበር።

ሐዋርያትና ሌሎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞሉ ሰዎች ፤ ወንጌልን ለመስበክ ወጡ። ከእነርሱም አንዱ ፊልጶስ ነበር፣ እርሱም በሰማርያ አስደናቂ መነቃቃትን ያመጣ ታላቅ አገልግሎት ነበረው። ሰዎችም ያመኑበትና በጌታ በኢየሱስ ስም የተጠመቁበት ቦታ ነበር (ሐዋርያት ሥራ 8:16)።

ወንጌላዊው መነቃቃቱን ትቶ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በነቢዩ ኢሳይያስ 53 ላይ ያለዉን እያነበበ ከነበረዉ ኢትዮጵያዊ ሰው ጋር ተቀላቀለ (ሐዋርያት ሥራ 8:26-39)። “ፊልጶስም አፉን ከፈተ፣ ከዚሁም መጽሐፍ ጀምሮ ኢየሱስን ሰበከለት” (ቁ. 35)። ስብከቱ የተመሠረተው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚሰጠው መዳን አስቀድሞ በተነገረበት ትንቢታዊ ቃል ላይ ነበር።

በስብከቱ መካከል አድማጩ የእግዚአብሔርን ሰው አቋርጦ “እነሆ ውሃ አለ። እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?”(ቁ. 36) አለ። ሁኔታው ተሟልቷል። ፊልጶስ ከጌታ ቃልና ከሐዋርያት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ እርምጃ ወሰደ፣ “በሙሉ ልብህ ብታምን ትችላለህ”(ቁ. 37) ብሎ ጠየቀ። መልሱም በድንገት “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ!” የሚል ነበር። እንዴት ያለ አስደናቂ ለውጥ ነው!

“ሰረገላውም እንዲቆም አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባውም ሁለቱም ወደ ውሃው ወረዱ፤ እሱም አጠመቀው” (ቁ. 38) ። እምነት በመስበክ መጣ፣ ስብከቱም ከእግዚአብሔር ቃል ነው። መንፈስ ወደ አድማጩ ልብ ገባ፣ እርሱም የመጠመቅ ፍላጎቱን ገለጸ።

ጴጥሮስ በልዩ ራእይ ወደ ቂሳርያ ይኖር ወደነበረው የሮማው መቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ቤት ተመራ። ስብከቱ ከመጀመሪያው እንደነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ውጤቶችን አሳይቷል። እንዲህ ተብሎ ተመዝግቦ እናገኘዋለን፣ “ጴጥሮስ ገና እነዚህን ቃላት ሲናገር፣ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ ወረደ” (ሐዋርያት ሥራ 10:44)። ቃሉ በሚሰበክበት ቦታ መንፈስ እንደሚንቀሳቀስ እናያለን።አማኞች ሁሉንም ጽድቅ መፈጸም እና ጌታ ያዘዘውን ሁሉ ማድረግ ይገባቸዋል. ሐዋርያውም እንዲህ አለ፣ “እነዚህ ደግሞ እንደ እኛ  መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን የሚከለክል ማን ነው?” አላቸው። በጌታም ስም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው” (ቁ. 47-48)። ዛሬ እያንዳንዱ እውነተኛ አገልጋይ ተመሳሳይ ስርዓትን ይከተላል እና እያንዳንዱ አማኝ መንፈስ ቅዱስን አስቀድሞ ቢቀበልም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ለመጠመቅ ይፈልጋል። ከእግዚአብሔር የሚመጣው ሁሉ ምንም ሳይለወጥ ይቀጥላል።

በመጻሕፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የሕፃናት ጥምቀት ወይም ሕፃናትን መርጨት የሚጠቁም ምንም ፍንጭ የለም። እንዲህ ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልማዶችን ሉቃስ 18፡ 15-17ን በመጥቀስ ለማጽደቅ የሚሞክር ሁሉ፣ በማቴዎስ 19:13-15 እና በማርቆስ 10:13-16 ያሉትን ተመሳሳይ ጥቅሶች ማንበብ አለበት። ምንም ጥርጥር የለውም፣

ጌታችን ኢየሱስ ወደ እርሱ የመጡትን ሕፃናት ብቻ እንደባረካቸው ግልጽ ነው። እጁን በላያቸው ጭኖ ወደ እቅፉ ወሰዳቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለማንኛውም ጥምቀት ወይም መርጨት ምንም ማጣቀሻ የለም። ዛሬም ቢሆን፣ አማኝ ወላጆች ሕፃናትን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ፣ ለጌታ እንዲቀርቡና እንዲሰጡ እንዲሁም በስሙ እንዲባረኩ።

እንዲሁም የሕፃናት ጥምቀትን ለመደገፍ በስህተት የሚተረጎመው ሌላው ጥቅስ ስለእሱ አንድም ቃል አይናገርም። ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ከተማ ታስረው ሳለ፣ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር ተከሰተ። የወህኒው ጠባቂ እስከ ሞት ድረስ ፈርቶ መጣና የእግዚአብሔርን ሰዎች፣ "ጌቶች ሆይ፣ እድን ዘንድ ምን ማድረግ አለብኝ?" ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፣ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተሰብህ ትድናላችሁ" አሉት (የሐዋርያት ሥራ 16:30-31)። በሚቀጥለው ጥቅስ ላይ ስለ ሂደቱ ተነግሮናል "የጌታን ቃል ለእርሱና በቤቱ ለነበሩት ሁሉ ተናገሩ።" ትዕዛዙ ከመጀመሪያው ተልእኮ ጋር እንዴት በትክክል እንደተጠበቀ እንገነዘባለን። ጥምቀት ከመፈጸሙ በፊት፣ ቃሉ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፣ መጀመሪያ ተሰብኮ ነበር፣ እና እነዚያ አድማጮች አመኑ ከዚያም ተጠመቁ። ስለ ወህኒው ጠባቂ እንዲህ እናነባለን፣ "በዚያችም ሰዓት ወሰዳቸው፣ ቁስላቸውንም አጠበ፣ እርሱና ቤተሰቡም ወዲያውኑ ተጠመቁ" (ቁ. 33)። እባክዎን ያስተውሉ፡ መጀመሪያ ስብከቱ መጣ፣ ሁሉም ሰሙት፣ ከዚያም አመኑ፣ እና ከዚያ በኋላ ብቻ ተጠመቁ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለ ሕፃናት ምንም አልተባለም።

ዛሬ ጥምቀት በአጠቃላይ የሚፈጸምበት መንገድ ሁሉም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይጎድለዋል። ይህ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተረጋገጠ ነው። ይህ ዓይነቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ጥምቀት የመጣው መላው ሕዝቦች በኃይል ክርስቲያን ከሆኑበት ዘመን ጀምሮ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ በቤተሰብ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው፣ ሕፃናትን ጨምሮ፣ በግንባሩ ላይ በሦስት የውኃ ጠብታዎች ይነካ ነበር። እምነት ተተካ፣ እና መጽሐፍ ቅዱስ ምንም የማይናገርባቸው የክርስትና አባቶች እና እናቶች ተሾሙ። አስቀድመን ካሳየነው ማየት እንደሚቻለዉ ግለሰቡ በእግዚአብሔር ፊት የግል ውሳኔ ማድረግ አለበት። ዛሬ በክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያለው ስብከት ከሐዋርያዊው ስርዓት ጋር እንደማይመሳሰል እና ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ውጤቶችን እንደማያመጣ መናገር ያሳዝናል።

### ስሙ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ማቴዎስ 28:19 የተሳሳተ ትርጓሜ እና አላግባብ ጥቅም ላይ የዋለ ሌላ ጥቅስ የለም፣ ይህም እንዲህ ይላል፣ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።" ለመረዳት የማይቻል ግን እስካሁን እውነት የሆነ ፤ በሦስተኛው ክፍለ ዘመን እነዚህን ቃላት ሙሉ በሙሉ ተሳስተው ተረድተው ነበር፣ እናም ዛሬም እየተተገበረ ያለ የሥላሴ

ቀመር ተፈጠረ። ጌታችን ስለ ስሙ እንደተናገረ ማንም የሚያስተውል አይመስልም። የምንጠመቅበት ይህ ስም ምንድን ነው? አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የተለያዩ መገለጦች ይገልጻሉ። ነገር ግን ከመጠመቃችን በፊት ስሙን ማወቅ አለብን። አንድ ሰው ብዙ ነገሮች ሊሆን ይችላል፡ አስተማሪ፣ ጠበቃ፣ ዳኛ፣ ወዘተ። አንድ ሰው አባት፣ ወንድ ልጅ፣ ባል ሊሆን ይችላል — ብዙ ነገሮች። እነዚህ የዚያ ሰው የሥራ መግለጫዎች ናቸው እና ቦታ አላቸው ፤ነገር ግን ከቦታቸዉ ጋር በትክክለኛው መያያዝ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸዉ። ነገር ግን ሁሉም ሰው፣ አስተማሪም ይሁን ጠበቃ ወይም ዳኛ፣ ወዘተ. ስም አለው። ብዙ ነገሮች የሆነው እና በብሉይ ኪዳን እራሱን በቃል ኪዳን ስሙ ያህዌ ብሎ በገለጠው በእግዚአብሔርም ዘንድ እንዲሁ ነው። በውሃ ጥምቀት፣ የአዲስ ኪዳን የቃል ኪዳን ስሙን ማወቅ አለብን። በማቴ. 28 ላይ፣ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ብሎ ራሱን በገለጠበት ስም እንዲያጠምቁ ትእዛዝ ብቻ ተሰጥቷል። ነገር ግን ስሙ ራሱ እዚያ አልተጠቀሰም።

አሁን ስሙ ብቻ የተጠቀሰባቸውን በርካታ የመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመለከታለን። ይህ እውነትን ለሚፈልጉ ሁሉ ታላቅ እርዳታ ይሆናል። በሉቃስ 10:17 ላይ "ሰባዎቹም በደስታ ተመለሱና፣ ጌታ ሆይ፣ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል" ብለው ተናገሩ። ስሙን ባይናገሩም እንኳ የኢየሱስን ስም ኃይል እንደሚያመለክቱ በራሳችን አንረዳም? በእርግጥ! በአንድ ወቅት ጌታችን "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እኔ እሆናለሁና "(ማቴ. 18:20) ብሏል። ባይናገርም እንኳ የኢየሱስን ስም ማለቱ እንደሆነ ማን ይጠራጠራል? በሉቃስ 24:47 ላይ "ንስሐና የኃጢአት ስርየትም በስሙ ከኢየሩስአሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበክ ዘንድ" የሚል እናነባለን። እንዲህ ያሉትን ጥቅሶች ሲያነብ የትኛው ስም እንደሆነ ሁሉም ያውቃል። በዮሐንስ 2:23 ላይ "ያደረጋቸውን ተአምራት ባዩ ጊዜ ብዙዎች በስሙ አመኑ" የሚለውን መግለጫ እናገኛለን። ማቴ.28:19ን ሲያነቡ ካልሆነ በስተቀር እንዲህ ያሉትን የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሲያነቡ የትኛው ስም እንደሆነ ሁሉም ማወቁ በጣም እንግዳ ነገር ነው! ያ በራሱ እንግዳ ነገር ነው። ይህንን በደንብ ማሰብ ያስፈልጋል።

እስካሁን በተጠቀሱት የመጻሕፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ የወልድን ስም የሚያመለክቱ የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶች ታይተወል፣ ነገር ግን በሚከተለው ውስጥ የአብን ስም የሚያሳዩ የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶች እናሳያለን። አሁን በእግዚአብሔር መግለጦች ልዩ መሬት ላይ እየተጓዝን ነው። ጌታ "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ" (ማቴ. 6:9) ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል። ይህን ጸሎት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በየእሁዱ ይደግሙታል፣ ማንም ስለሚቀደሰው የአብ ስም ሳያስብ ወይም ሳይጠይቅ። በዮሐንስ 12:28 ላይ ወልድ "አባት ሆይ፣ ስምህን አክብረዉ" አለ። ከዚያም ከሰማይ ድምፅ መጣና "አክብሬዋለሁ፣ ደግሞም አከብረዋለሁ" አለ። ስለ የትኛው ስም ነበር የሚናገረው? ስሙን ያከበረውና ደግሞም የሚያከብረው የእግዚአብሔር ስም ማን

ነው? እግዚአብሔርን ልንቀርብበት የምንችለው አንድ ስም ብቻ ነው፣ እርሱም የራሱ ስም ነው።

በጸሎቱ ውስጥ፣ ወልድ እንደገና አብን ጠቅሶ "ከዓለም የሰጠኸኝን ሰዎች ስምህን ገልጬላቸዋለሁ"(ዮሐንስ 17:6) አለ። ይህ ማነኛዉን የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስምን ነዉ የሚያመለክተዉ? በእርግጥ አይደለም! ይህንን ሲያነብ ትኩረት የሰጠ ሁሉ የአብ ስም ከዚህ ዓለም ተዋጅተዉ ለጌታችን ለተሰጡት እንደተገለጠ ማስተዋል ነበረበት። እነርሱም የእግዚአብሔር እውነተኛ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናቸው። እግዚአብሔር ያውቃቸዋል፣ እነርሱም እግዚአብሔርን ያውቁታል። አሁን ጉዳዩን ወደ አንድ የጋራ መለያ ማምጣት አለብን። "ቅዱስ አባት ሆይ፣ እኛ አንድ እንደሆንን እነርሱም አንድ እንዲሆኑ የሰጠኸኝን በራስህ ስም ጠብቃቸው" (ዮሐንስ 17:11)። ከዚህ የበለጠ ግልጽ ሊሆን አይችልም፡ የወልድ ስም የአብ ስም ነው! ስለዚህ በቁጥር 26 ላይ "ስምህንም አስታወቅኋችሁ፣ ደግሞም አስታዉቃቸዉማለሁ" የሚል እናነባለን። እኛ የምንመለከተው አንድ ስም ያለው አንድ አምላክን ብቻ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ "እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፥ አልተቀበላችሁኝምም" (ዮሐ.5:43) ብሏቸዋል። የዛሬዎቹ ክርስቲያኖችስ? የአብና የወልድ ስም አንድ መሆኑን አውቀው ይቀበሉታልን? አብ በወልድ እንደተገለጠና ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ማለትም ኢየሱስ — አማኑኤል — እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው! ብሎ የገለጠልንን የሚያምን የተባረከ ነው። የእግዚአብሔር አንድ የግል መገለጥ ብቻ ነው ያለው ፤ እርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ ሆኗል። አንድ የእግዚአብሔር ስም ብቻ ነው ያለው እርሱም ሊገለጥልን የሚገባው ስም ነው፡ ያ ስም **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ነው። በዚህ ስም ወደ አብና ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብ እንችላለን። ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል ፤ እና ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራል! እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ተገናኘን፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻም ከእርሱ ጋር መገናኘት እንችላለን። በእነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች ብርሃን የመጽሐፍ ቅዱስ ማቴዎስ 28:19 ችግር መፈታት አለበት። እዚያ ላይ ስሙ ሳይጠቀስ ስለ ስሙ ይናገራል፤ በኋላም የዚህ አንድ ስም የሆኑት ማዕረጎች ተትተዋል ፤ የውሃ ጥምቀት በሚሰጥበት ጊዜም ስሙ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

## የሐዋርያት ትምህርት

አሁን ጥምቀት በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሲፈጸም እንደነበር እንመለከታለን። ጌታ ታላቁን ትዕዛዝ ሲሰጥ ከሰሙት ሰዎች መካከል ጴጥሮስ አንዱ ነበር፣ በማቴዎስ 28 ላይ እንደተጻፈው። ኢየሱስ የመንግሥቱን ቁልፎች የሰጠው ለእርሱ ነበር፣ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ማግኘት እንደሚችል ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ ከመውረዱ በፊትም እንኳ በ120ዎቹ መካከል ተነሥቶ እነዚያን ክስተቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማነፃፀር ማስቀመጥ ጀመረ (የሐዋርያት ሥራ 1:15)። በብዓለ ኃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ ወዲያውኑ

ለተሰበሰቡት ሕዝቦች ሰበከ:: “ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፣ ጴጥሮስንና የቀሩትን ሐዋርያትም፡- ወንድሞች ሆይ፣ ምን እናድርግ? አሏቸው” (የሐዋርያት ሥራ 2:37):: ዛሬም ተመሳሳይ ወንጌልና ተመሳሳይ ክርስቶስ በሚሰበክበት ሁሉ፣ ልቦች ይነካሉ፣ ተመሳሳይ ጥያቄ ይነሳል፣ ተመሳሳይ መልስም መሰጠት አለበት፡- “ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፡- ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁ ይሰረይላችሁ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ” (ቁ. 38):: ይህ ታላቁ ትዕዛዝ በተግባር የዋለበት የመጀመሪያ አጋጣሚ ነበር:: ያመኑትም ሰዎች በማቴዎስ 28:19 መሠረት ጌታ ወደተናገረው ስም በትክክል ተጠመቁ::

ማንም ሰው በማዕረግ እና በስም መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል::ኢየሱስ የተናገረዉ ቃል ሐዋርያት ከተናገሩት ቃል የበለጠ ጠቀሜታ እና ክብደት አለዉ  የሚለው ክርክር እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው አይማርክም:: በእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ መላው መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም መለኮታዊ መነዳት መጻፉ እና ፍጹም ምንም ስህተት የሌለዉ መሆኑን ያምናል:: ማንም ሰው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ቅራኔ ካነበበ፣ ያ ቅራኔ በእራሱ አእምሮ ውስጥ እንጂ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንዳልሆነ ማመን አለበት! መንፈስ ሐዋርያትን ታላቁን ትዕዛዝ እንዲፈጽሙ እንዴት እንደመራቸው ማየታችን በጣም ደስ ይላል::

ሰዎች በሰማርያ እንዳመኑና እንደተጠመቁ አስቀድመን ጠቅሰናል:: የዚህ መነቃቃት(ሪቫይቫል) ዜና ወደ ኢየሩሳሌም ደረሰ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ እንዲህ እናነባለን፡ - “በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትም ሰማርያ የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበለች በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ እነርሱ ሰደዱ:: እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ አልወረደም ነበርና ፤ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጅ” (የሐዋርያት ሥራ 8:14-16):: ትኩረቱ በጌታ በኢየሱስ ስም መጠመቃቸው ላይ ነው:: በጣም እንግዳ ነገር ነውን? ምናልባት አይደለም!

በቆርኔሌዎስ ቤት የነበሩት ያመኑት ሰዎች በጌታ ስም እንዲጠመቁ ያዘዘው ጴጥሮስ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 10:48) :: በአዲስ ኪዳን ስለ ውሃ ጥምቀት ባለው ትምህርት ውስጥ ያለውን አስደናቂ ቀጣይነት ማየት እንችላለን:: ይህንን ሊክድ የሚችል የስነ-መለኮት ምሁር የለም፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ራሱ ስለእርሱ ይመሰክራል:: ጳውሎስም እንዲህ እስከ ማለት ደረሰ፡- “ነገር ግን እኛ ወይም ከሰማይ መልአክ ፤ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን” (ገላ. 1:8) ::

በሁሉም ሁኔታዎች ጥምቀት የተከናወነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መሆኑን ሁሉም አስተውሎ ይሆናል:: ሐዋርያት ጌታ የተናገረውንና ያዘዘውን በትክክል ተረድተው ነበር:: ሁሉንም ነገር በትክክል እንደ ጌታ መመሪያ ፈጸሙ:: ትዕዛዙ ቀስ ተብሎ፣ በጥንቃቄ፣ እና በጸሎትም መነበብ አለበት፡- “ስለዚህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ

ቅዱስ ስም እያጠመቃችኊቸው ፤ያዘዝኊችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኊቸዉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።" አሁን፣ አባት ስም አይደለም፣ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስም ስም አይደለም። እነዚህ የአንድ አምላክ የተለያዩ መገለጦች መግለጫዎች ናቸው። ሐዋርያት የተማሩት በጌታ በራሱ ነው፣ ከትንሣኤው በኋላ ባሉት አርባ ቀናት ውስጥም ጭምር። እርሱ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገሮች ሁሉ ተናግሯል፣ በእርግጥም ጥምቀት ከዋና ትምህርቶች አንዱ ነው። እነርሱ እግዚአብሔር ራሱን አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሆኖ የገለጠበትን ስም አዉቀዉታል። ይህ እውነተኛ አማኞች የሚጠመቁበት ስም ነው። በትክክል የታዘዙትን አደረጉ። ቢያንስ የተለያዩ መግለጫዎች ጋር የተገናኙትን የማዕረግ ስሞች እና ለመዳናችን የተሰጠውን ስም መለየት ችለዋል።

አሁን ጌታችን በቀጥታ መገለጥ የተለየ እቃ አድርጎ ወደ መረጠዉ ወደ ጳውሎስ እንመጣለን። እርሱ እንዴት አጠመቀ? ወደ ኤፌሶን በመጣ ጊዜ የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ የሚያውቁ አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት አገኘ። ከዚያም እንደ ድነት ዕቅድ መመሪያ ሰጣቸዉ ወዲያውኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ውጤት ታየ፡- "ይህን በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ" (የሐዋርያት ሥራ 19:5)።

ሁሉም ነገር ቢያንስ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች መረጋገጥ አለበት። በኢየሩሳሌም፣ በሰማርያ፣ በቆርኔሌዎስ ቤት፣ እንዲሁም በኤፌሶን ምን እንደተከሰተ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተናል፤ አይሁዶች ሆኑ ሳምራዊ፣ ወይም አሕዛብ፣ ጴጥሮስ፣ ፊልጶስ ወይም ጳውሎስ ይሰብኩ የነበረ ቢሆንም፣ በሁሉም ቦታ ጥምቀት የተከናወነው **በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ** ስም መሆኑን እንገነዘባለን።

ቀደም ሲል እንደገለጽነው፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እርስ በእርስ መጣረስ ሊኖር አይችልም። የእግዚአብሔር መንፈስ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሁለት ወይም ሦስት የተለያዩ መገለጦችን ፈጽሞ አይሰጥም። እግዚአብሔር በዚያ የመጀመሪያው ትውልድ ውስጥ የራሱን ሰዎች መርጦ ነበር። ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ፣ ወይም ሌሎች ሰዎች ቢሆኑም፣ ተመሳሳይ ወንጌልን ሰበኩ እና በተመሳሳይ መንገድ አጠመቁ። ይህ የሆነው ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ሁሉ ጋር በፍጹም ስምምነት ነው። ከኢየሱስ ጋር ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን ሰዎች እና ጌታን በደማቅ ብርሃን የተገናኘውን ጳውሎስን ጌታን በተሳሳተ ሁኔታ ተረድተዉ እና በተሳስተ መንገድ እያጠመቁ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ስትቋቋም በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መናፍቅነትን አስተዋወቁ ለማለት የሚደፍር ማን ነው? እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ከስድብ አይተናነስም።

ጳውሎስ ለሮማውያን ሲጽፍ ደግመን እንሰማለን፡- "ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን ሁላችን ወደ ሞቱ እንደተጠመቅን አታውቁምን?" (ምዕራፍ 6:3)። እዚህ ላይ እራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከተጠመቁት ጋር ያካትታል። አንተ እንዴት ተጠመቅህ? በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንድ ሰው በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማዕረጎችን

በመጠቀም በሥላሴ ቀመር የተጠመቀበት አንድም ክስተት አልተመዘገበም። ይህ እውነታ በደንብ በትኩረት መታየት ይገባዋል።

ለአገልግሎት የተጠሩትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሁሉ ተመሳሳይ ግንዛቤ፣ ተመሳሳይ ትምህርት፣ ተመሳሳይ እምነት፣ ተመሳሳይ ጥምቀት፣ ወዘተ ነበራቸው። ሁሉም ከጌታ፣ ከቃሉ፣ እና እርስ በእርሳቸው ጋር ፍጹም ስምምነት ነበራቸው። አንድም ሰው ማቴዎስ 28ን አልደገመም። "...በአብ ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም (ስሞች አይድለም ፤ ነገር ግን ስም) እያጠመቃችኋቸው..." ተብሎ የተነገረው በነጠላ ቁጥር እንጂ በብዙ ቁጥር እንዳልሆነ ያውቁ ነበር። ጌታችንም "በወልድ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም" ማለቱን አልቀጠለም። የስሙ አንድ መጠቀስ ብቻ ነው ያለው፣ ያም በነጠላ ቁጥር ነው። እግዚአብሔር ራሱን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እንደገለጠ ያምኑ ነበር። እናም ከእነዚህ ሦስት መገለጦች ጋር የሚሄደውን ስም አወቁ። እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ኅብረት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። ምንም ዓይነት ሥነ-መለኮታዊ ተጽዕኖ አልነበረባቸውም፣ የራሳቸውንም ትርጓሜ አልሰጡም። መለኮታዊ መገለጥ ነበራቸው።

ማንም ሰው የማቴዎስ 28ን ቃል ብቻ ከመገለጥ ውጪ ከወሰደ፣ የትዕዛዙ ዓላማ ምን እንደሆነ ሳይረዳ ቁጥር 19ን ደጋግሞ ይናገራል። ማቴዎስ 28 እና ማርቆስ 16 የጌታን የመጨረሻ እና ታላቅ ትዕዛዝ ያመለክታሉ፣ ይህም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሲፈጸም እናገኘዋለን። ያ ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እስካለች ድረስ ለዘላለም ትክክለኛ መለኪያ እና ብቸኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሠራር ነው።

ለምሳሌ፣አንድ አስተማሪ ለተማሪዎች ጥያቄ ቢያቀርብ ፣መልሱን፣ውጤቱን፣ እንጂ የሂሳብ ጥያቄዉን መደጋገም በእርግጠኝነት አይጠብቅም። አንድ አስተማሪ "3 x 3 ስንት ነው?" ብሎ ቢጠይቅ እና መልሱም "3 x 3 = 3 x 3" ቢሆን፣ መልሱ ስላልተሰጠ አንድ ሰው የሆነ ችግር እንዳለ ያውቃል። ወደ ጥምቀት ሲመጣ አስተማሪዎችም ሳይቀሩ ችግሩን ይደግማሉ እንጂ መልሱን አይሰጡም። ጌታ የተናገረውን ከማድረግ ይልቅ፣ የተናገረውን በቃል ይደግማሉ። እንደ ሐዋርያት ካደረግን ብቻ፣ ተመሳሳይ ጌታ ተመሳሳይ ወንጌል እንድንሰብክ እንደጠራን ማረጋገጫ ይኖረናል። የሐዋርያት እና የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች ትዕዛዙን ተረድተው በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም መገለጥ መሠረት ፈጸሙት። የጽሑፍ ምስክርነት ስላለን እግዚአብሔር ይመስገን። እኛ የሚያስፈልገን ሐዋርያት እንዳዩት እንድናይ፣ እንዳስተማሩት እንድናስተምር፣ እና እንዳጠመቁት እናጠምቅ ዘንድ ተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ተመሳሳይ ብርሃን ብቻ ነው።

ይህ ትንተና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። ሁሉም ሰው በቁም ነገር ሊመለከተው ይገባል። ብዙውን ጊዜ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ ቢመስሉም፣ አንድ አይደሉም። እርስ በእርሳቸው ቅርብ ቢመስሉም፣ በተመሳሳይ ጊዜ ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ እርስ በእርሳቸው ሊራራቁ ይችላሉ። የጌታን ስም መካድ የለብንም። ለፊላዴልፍያ

ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ተብሎ ነበር፡- “…ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፤ ስሜንም አልካድህምና” (ራዕይ 3:8)። ስለ ኢየሱስ ስም ውብ መዝሙሮችን ስለሚዘምሩ፣ ያንን ስም በጸሎታቸው ስለሚጠቀሙ፣ ስለዚያ ስም በኃይል ስለሚሰብኩ፣ ከዚያም ወደ መጨረሻው ፍጥጫ ሲመጣ ግን ያንን ስም ክደው በጥምቀት ከእርሱ ጋር መያያዝ የማይፈልጉ አማኞችስ? የጋራ ግንዛቤ እንዲህ ባለ ሁኔታ የሆነ ችግር እንዳለ ይነግረናል።

አጋንንትን ለማስወጣት፣ ለበሽተኞች ለመጸለይ፣ በዚያ በኃይለኛ ስም ተአምራትን ለማድረግ የኢየሱስን ስም ስለሚጠቀሙ ታላላቅ ወንጌላውያንስ? ፤ ከዚያም በዚያ በብዙ በሚጠቀሙበት ስም ለመጠመቅ ሲወስኑ ግን ይከለክላሉ አልፎ ተርፎም ይዋጋሉ? በከንፈራቸው የኢየሱስ ስም ምን ያህል ድንቅ እንደሆነ ይመሰክራሉ፣ ነገር ግን በእውነቱ ስሙን ራሳቸው አላወቁትም፣ እናም በኢየሱስ ስም የሚመጣዉን ነቀፌታ ለመሸከም ዝግጁ አይደሉም። ስለ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጌታ በማቴዎስ 7:22-23 ላይ አስቀድሞ ተናግሯል፡- “በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። ያን ጊዜም፡- እናንተ ክፉት የምትሠሩ ከእኔ ራቁ፤ ከቶ አላወቅኋችሁም እላቸዋለሁ።”

ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ስለሙሉ ወንጌል አማኞች ነው። በአንድ በኩል ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡትን በረከቶችና ተስፋዎች የሚካፈሉ ናቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ባሉና በባህላዊ ትምህርቶች ውስጥ ነዉ ያሉት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ እርማትን ለማየት ዝግጁ አይደሉም። ሁሉም ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ሁሉ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን የለበትም? ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ለመቆም እና የባህላዊ፣ ቤተ እምነታዊ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነውን የጥምቀት ልምምድ ለመካድ ድፍረት ይጠይቃል። በአዲስ ሕይወት ትንሣኤ ከእርሱ ጋር አንድ ለመሆን ከፈለግን በጥምቀት ከክርስቶስ ሞት ጋር ራሳችንን አንድ ማድረግ አለብን (ሮሜ 6:3)።

## መናፍስትን መለየት

አንድ በጣም ጠቃሚ ነገር መንካት አስፈላጊ ነው። በዛሬዎቹ ባህላዊ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እውነተኛ መለወጥ እና አዲስ ልደት የሚለው ትምህርት እምብዛም አይገኝም። ይህ ቃል ጥቅም ላይ ቢውልም፣ ልምዱ ራሱ የጎደለ ነው። ነገር ግን የሙሉ ወንጌል አማኞችነን በሚሉ ስብስቦች ውስጥም እንኳ መሠረታዊ ትምህርቶች በጥንቃቄ አይመረመሩም። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችና የሰለጠኑ የሥነ-መለኮት ምሁራን እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥምቀት እንዴት መፈጸም እንዳለበት ማየት እንዴት ሊሳናቸው ይችላል? አንድም ሰው በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ቀመር ተጠምቆ የማያውቅ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እርማት የማይቀበሉት ለምንድን ነው?

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት የተፈለሰፈውንና የተዋወቀውን ጥምቀት ይተገብራሉ። አሳዛኝ ነገር ግን እውነት ነው፣ ከተሃድሶው ዘመን ጀምሮ የተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ ተመሳሳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ጥምቀት መጠቀም ጀመሩ።

አብዛኛው ሰው "በምዕራባዊው ዓለም" ውስጥ ተመሳሳይ ቀመር በአስማት፣ በመናፍስታዊ ልምምዶች ውስጥ ጥቅም ላይ እንደሚውል ሲያውቅ ሊደነቅ ይችላል፣ ይህም ሦስቱ ከፍተኛ ስሞች ወይም ቅዱስ ቀመር ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በመናፍስት ጠሪዎች ሙታን መናፍስት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በጥንቆላ ውስጥም እንኳ ጥቅም ላይ ይውላል። ተመሳሳይ ቀመር አንዳንድ ማኅበራት ሲቀላቀሉ መሐላ ሲገቡ ጥቅም ላይ ይውላል። በእነርሱ ውስጥ ሲሳተፉ የሚጠራጠሩ ሰዎች "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" የሚለውን ቀመር ሲሰሙ ትንሽ ጥሩ ስሜት ይሰማቸዋል። ጥንቆላ ሲሠሩ እንኳ፣ ይህ ቀመር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለተጠቀሙበት "ከእግዚአብሔር የመጣ መሆን አለበት" ብለው ያስባሉ። በጥቁርም ሆነ በነጭ አስማት፣ "የሙሴ ስድስተኛና ሰባተኛው መጽሐፍ" በሚባለው በመጠቀም በየትኛውም ቦታ ተመሳሳይ ቀመር ጥቅም ላይ ይውላል።

ስለ እንደዚህ ዓይነት ልምምዶች እነዚያን ሰዎች ቢያነጋግሩ፣ መልሳቸው "ይህ ስህተት ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ስም ነው የሚደረገው" ነው። አይደለም፣ በጭራሽ! በኢየሱስ ስም የተደረገው ብቻ በእውነት በእግዚአብሔር ስም የተደረገ ነው። ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ የዚህ ዓለም አምላክ ከሆነው ከሰይጣን ናቸው። ጌታችን እንደ ጠረጴዛ መገልበጥ፣ በካርታ መተንበይ የመሳሰሉት፣ ጥንቆላ፣ የዘንባባ ዕውቀት ወዘተ ከመሳሰሉት ክፉ ልምምዶች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እነዚህ በቃሉ የተከለከሉ ናቸው። ነገር ግን በሃይማኖታዊ ሽፋንና በዚያ ቀመር ስለሚደረጉ፣ ሰዎች በእነርሱ ይታለላሉ። አስማታዊ ልምምዶች፣ መንፈሳዊነት፣ ወዘተ ከእግዚአብሔር ቃል በሚያስፈልገው እውነተኛ ተግባር ጋር ምን የሚያመሳስላቸው ነገር አላቸው? የእግዚአብሔር አገልጋዮችና የሰይጣን መሣሪያዎች አንድ ነገር መናገር የጀመሩት መቼ ነው? የሰይጣን መንግሥት በእግዚአብሔር መንግሥት መካከል መግባት የጀመረው መቼ ነው?

ሁለት ሰዎች አንድ አይነት ነገር ሲያደርጉ ተመሳሳይ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጥያቄ ሁሉም ሊጋፈጥ ይገባል። ይህን ቀመር ሲጠቀሙ የተለያዩ ነገሮችን የሚያደርጉ ሰዎችን ሲሰሙ አንዳንዶች ይደነቃሉ፣ ምናልባትም ግራ ይገባቸዋል። ነገር ግን ተመሳሳይ ቀመር ለሚባለው "ጥምቀት" እና ለሌሎች ሃይማኖታዊ ልምምዶች ሲውል፣ ሁሉም ትክክል ሆኖ ያገኙታል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ሁሉ እና የሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል በኢየሱስ ስም ይፈጸማል። ስለዚህ

በቆላስይስ 3:17 ላይ "የምትሠሩትን ሁሉ በቃልም ሆነ በሥራ ሁሉን በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" የሚለውን እናነባለን።

አሁን ማንም ነቢይ እና ሐዋርያ ምንም አይነት ቀመር ተጠቅሞ እንደማያዉቅ አዉቀናል፣ ነገር ግን አዳኙ በጥምቀት የተናገረውን ስም ብቻ ነው። "እግዚአብሔር እና ከሰው ልጆች ጋር ያለዉ ዕቅድ" በሚለው ብሮሹሬ ውስጥ አንድ እውነተኛ እግዚአብሔር በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ በአንድ ስም **በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ** እንደተገለጠ በግልጽ ታይቷል። ማቴዎስ 28:19 ፍጹም እውነት ነው፣ እንዲሁም የሐዋርያት ሥራ 2:38 እና ሁሉም ሌሎች ጥቅሶች። የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛው መንገድ መረዳት ብቻ ነው የሚያስፈልገን። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ከመጀመሪያው ጀምሮ አሳስቶ ተጠቅሞበታል እና አሳስቶ ተርጉሞታል። ሰዎችን በሃይማኖታዊ መንገድ በተሳሳተ ጥምቀት ለማታለል ችሏል። በእውነቱ ይህ ማታለል ነው። ወደ ጌታ ሲመጣ "ተጽፏል..." አለ። ነገር ግን ጌታችን "ደግሞም ተጽፏል..." ሲል መለሰ። ሰይጣን ጥቅሶችን ከዓውድ አውጥቶ በዉሸት ተጠቀመባቸው። ተመሳሳይ ነገር በማስተማርና በማጥመቅ ትእዛዝ ላይ ይደረጋል። የእግዚአብሔርን ክብር በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንዳያዩ ፤ ሰይጣን የሰዎችን አይኖች አሳዉሯል (2 ቆሮ. 4:4-6) ። አዳኙ የተናገረው ስም ከእነርሱ ተሰውሯል።

መላው የክርስትና ዓለም በጨለማና በድንቁርና ተይዟል። ዛሬ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ወዴት ነው የምናገኘው? ዛሬ ባለው የሃይማኖታዊ ባቢሎን ውስጥ በራዕይ 18:4 መሠረት የሚወጣ ማን ነው? ለማየት ዓይን፣ ለመስማት ጆሮ፣ ለመረዳትም ልብ ያለው ማን ነው? በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃልና በሰው በተፈጠሩ ትርጓሜዎች መካከል መለየት የሚችል ማን ነው? እግዚአብሔር ሁልጊዜ ብርሃንን ከጨለማ ይለያል። መመሪያዎችን ለመቀበል፣ ለማመን፣ እና የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ለመተግበር ድፍረት ያለው ማን ነው? ሁሉም መንፈሳዊ ነገሮች በሥጋና በደም ሊታወቁ አይችሉም። አንዱ ሌላውን ማስተማር አይችልም። ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ፊት በግል ተጠያቂ ነው እና የራሱን ውሳኔ ማድረግ አለበት።

በመጨረሻም፣ የምክር ቃል። በክብር ውስጥ መሆን የሚፈልግ ሁሉ ይህንን ማወቅ አለበት፣ እግዚአብሔር የአለማወቅን ዘመን ትቶ፣ አሁን ግን ፍጹም ፈቃዱን በፍጹም ቃሉ ይገልጣል። እርሱ ሁሉም ሰው በእርሱ እንዲያምን እና በቃሉ መሠረት እንዲሠራ ይጠብቃል። ሁሉንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ትምህርቶችን መተው አለብን፣ ተወዳጅነታችንን እና ወዳጆቻችንን ብናጣም እንኳ። ወደ መጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ አሠራር እና ተግባር ለመመለስ ፈቃደኛ መሆን አለብን።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 3 ላይ እግዚአብሔር የመታደስ ዘመን እንደሚልክ እና ክርስቶስም ነገሮች ሁሉ ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው የሚመለሱበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ በሰማይ እንደሚቆይ የሚገልጽ ተስፋ እናነባለን። በቁጥር 19-21 ላይ "...ከጌታ ፊት

የመታደስ ዘመን በመጣ ጊዜ፣ አስቀድሞም የተሰበከላችሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ይልካል፣ እርሱም ነገሮች ሁሉ እስከሚመለሱበት ዘመን ድረስ ሰማይ ሊቀበለው ይገባል፣ ይህንንም እግዚአብሔር ከጥንት ዘመን ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ ሁሉ አፍ ተናግሯልና።" እዚህ ላይ ክርስቶስ የመታደስ ዘመንና የመመለሻ ዘመን እስኪመጣ ድረስ በክብር እንደሚኖር በግልጽ ተገልጿል። በግልጽ ቋንቋ፣ ይህ ማለት አሁን በመጨረሻው ዘመን፣ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት፣ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮች ሁሉ ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው መመለስ አለባቸው ማለት ነው።

ክርስቶስ ዳግም ይመጣል ብለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ስለዚሁ ጉዳይ ስብከት ሰምተዋል። በእርግጥ ብዙዎች የክርስቶስን ቅርብ መመለስ ይጠብቃሉ። ታዲያ ይህ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሊመልስ የሚፈልግበትና ከፊቱ የመታደስ ዘመን ሊሰጥበት የሚገባው ጊዜ መሆኑን ለምን አይገነዘቡም? ጌታና አዳኝ ያለዉ አንድ ፍላጎት ብቻ ፣ እርሱም ተዋጅተዉ የክርስቶስ አካልን ስለሚሰሩት ስለራሱ ሰዎች ያለዉ ሃሳብ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተች መሆን አለባት። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ጥምቀትና ሁሉም ሌሎች ትምህርቶችና ልምምዶች፣ ሐዋርያት እንዳደረጉት፣ ወደ ነበረበት የመመለሱ አካል ናቸው። ጳውሎስ በኤፌሶን 2:20 ላይ "...በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፣ ዋናው የማዕዘን ድንጋይም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው..." ሲል ጽፏል። ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን እስክትጠናቀቅና ወደ ቤቱ ሊወስዳት እስኪመለስ ድረስ ይገነባታል። ነገር ግን በመጀመሪያ ወደ መጀመሪያው ትምህርቶችና ልምምዶች መመለስ አለብን። ከዚያም ጌታ ይመጣና ወደ ክብር ይወስደናል።

ማንም ሰው ይህን ስለ ጥምቀት የቀረበውን ማብራሪያ እንደ ቀላል  ማየት የለበትም። እግዚአብሔር መሐሪ ከሆነልን፣ የእግዚአብሔር ቃል በሚጠይቀው ሁሉ ለመስማማት አስፈላጊ መሆኑን እናያለን፣ እናም በፈቃደኝነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠመቅ እንፈልጋለን። በዚህ መንገድ፣ ያረጀዉን ቀንበር በሁሉም ቤተ እምነቶች ላይ የተቀመጠውን እና በሥላሴ ቀመር የተጠመቁትን ሁሉ በመንፈሳዊ የሚያስረዉን እንሰብራለን። ከእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ ይሰማል እና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ያደርጋል። ይህንን ምክር ከልቡ በእዉነት የሚቀበል ብፁዕ ነው፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ሲመጣ ዝግጁ ለመሆን ለሚደረገዉ ዝግጅት አስፈላጊ ነውና። እርሱም ተስፋውን ይሰጣል፤ እርሱም ተስፋዉን ይፈጽማል።

## የጌታ እራት

ወደ ጌታ እራት ርእሰ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት፣ ስለ ፋሲካ ጉዳይ ማየት አለብን። በብሉይ ኪዳን ያለው ተፈጥሯዊ ነገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወደ ሆነዉ ልዕለ ተፈጥሮአዊው እውነታ ቀድሞ ይጠቁማል እና ይዋሃዳል።

ፋሲካ ዛሬም እንኳ በአይሁድ ማኅበር ውስጥ ከሚገኙት በጣም አስፈላጊ በዓላት አንዱ ነው። ጌታ ለእስራኤላውያን እያንዳንዱ ቤተሰብ ጠቦት በግ እንዲያርድ፣ ሥጋውንም እንዲበላ፣ ደሙንም በበሩ መቃ :- በግራ፣ በቀኝና በላይ እንዲቀቡ ነገራቸው (ዘፀ. 12) ። ማንም ሲገባ ደሙን እንዳይረግጠው የበሩ የታችኛዉ መቃ በደም መቀባት የለበትም።

"ፔሳሕ" የሚለዉ የእብራይስጥ ቃል ማዳን ወይም ማለፍ ማለት ነው። ሁሉም የግብፃውያን የበኩር ልጆች በፍርድ መልአክ ሲገደሉ፣ የእስራኤል የበኩር ልጆች ግን ዳኑ፣ ጌታም "ደሙም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙንም ሳይ ከእናንተ አልፋለሁ ፤ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም" (ዘፀ. 12:13) ብሎ ነበርና።

የእነዚያ በጎች ደም ለኃጢአታቸው ማስተስሪያ ፈሰሰ። በፍርድ ጊዜም የመጠበቃቸዉ ምልክት ነበር። በግብፃውያን ቤቶች ሁሉ ልቅሶና ሐዘን ነበር፣ ሙታን በየቦታው ነበሩና። በእስራኤላውያን ቤቶች ግን ፍጹም ደህንነት ነበር። የእግዚአብሔር ቁጣ ሊገባ አልቻለም፣ ምክንያቱም በጎች በእነርሱ ፋንታ ታርደው ነበር። በነጻነት መውጣት ችለዋል። ተመሳሳይ ነገር ለዳኑትም ይሠራል። የእግዚአብሔር ቁጣ በማያምኑት ላይ ሲመጣ ፤ የዳኑትም በአስፈሪው ፍርድ ሊነኩ አይችሉም። የእግዚአብሔር በግ ደም ለእኛ ማስተስሪያና መከላከያችን ነው። ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን "ክርስቶስ ፋሲካችን ነውና እርሱ ስለ እኛ ታርዷል" (1 ቆሮ. 5:7) ሲል ጽፏል። ነቢዩ ኢሳይያስም "...የደህንነታችን ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበር..." (ምዕራፍ 53:5) ይላል። በሞቱ ታረቅን፤ በደሙም ኃጢአታችን ተሰረየልን፣ የዘለአለም ሕይወትም አገኘን።

ጌታ በሙሴ በኩል ፋሲካን (ይህም የእስራኤላውያን ከግብጽ መውጣትን የሚያመለክት ነው) በልዩ ሁኔታ እንዲከበር አዘዘ፡- "ይህም ቀን ለመታሰቢያ ይሁንላችሁ፤ ለጌታም በዓል ታደርጉታላችሁ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለዘላለም በዓል አድርጋችሁ ጠብቁት" (ዘፀ. 12:14) ። ከቁጥር 26-27 ይህ እንደገና ተረጋግጧል፡- "ልጆቻችሁም ይህ አምልኮ ለእናንተ ምንድን ነው? ባሏችሁ ጊዜ እናንተ :- በግብጽ አገር በእስራኤል ልጆች ቤቶች ላይ አልፎ ግብፃዊያንን በመታ ጊዜ ፤ ቤቶቻችንን ያዳነ የእግዚአብሔር የማለፍ መሰዋት ይህች ናት ትሉአቸዋላችሁ።"

በተመሳሳይ መንገድ፣ የጌታ እራት የእኛን መቤዥት የምናስታውስበት ነው። **ጌታ** እስኪመለስ ድረስ ሊካሄድ ይገባል (1 ቆሮ. 11:26)። በአንድ በኩል ታላቁ የእርቅ ቀንን

ወደ ኂላ እንመለከታለን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዳግመኛ የተዋጀነዉ ሁሉ ቤዛችንን በክብር በታላቁ እራት ላይ የምንገናኝበትን የከበረ ቀን በጉጉት እንጠብቃለን፡፡ የጌታ እራትን ሲመሠርት ጌታ እንዲህ አለ፣ "...ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" (ሉቃስ 22:19) አለ፡፡ በጌታ እራት ስንካፈል የተጠናቀቀውን የቤዛነት ሥራ እናስታውሳለን እና ክርስቶስ አዳኛችን በመስቀል ላይ ደሙን ባፈሰሰ ጊዜ እንደተዋጀን በእያንዳንዱ ጊዜ እንደ አዲስ እናውቃለን፡፡

ምትክ ተደርጎ የታረደዉ በግ ያለእርሾ ከተጋገረ እንጀራ ጋር መበላት ነበረበት፡፡ ስለዚህ "ሰባት ቀን እርሾ የሌለበትን እንጀራ ትበላላችሁ፤ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እርሾን ከቤታችሁ ታወጣላችሁ፤ ከመጀመሪያዉ ቀን ጀምሮ እስከ ሰባተኛው ቀን ድረስ እርሾ ያለበትን እንጀራ የሚበላ ነፍስ ሁሉ ከእስራኤል ተለይቶ ይጠፋልና" (ዘፀ. 12:15) የሚለውን እናነባለን፡፡ ይህ ትዕዛዝ መከበር እና በታዘዘዉ መሠረት መፈጸም ነበረበት፡፡

የፋሲካ በዓል አከባበር ሰነስርአት የተመሰረተዉ እና የተጅመረዉ በቀጥታ ነፃ ከመሆናቸዉ እና ከግብጽ ከመውጣታቸው በፊት ነበር፡፡ የጌታ እራት አከባበር ስነስርአት የተመሰረተዉ እና የተጀመረዉ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እያከበረ በነበረዉ የፋሲካ በዓል ላይ ሲሆን፣ቤተክርስቲያን ወደ ተዋጀችበት የመሰዋት ስራ ከመሄዱ በፊት ነበር ፡፡ "ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ እርሱ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር በማዕድ ተቀመጠ፡፡ እርሱም፡- ከመከራዬ በፊት ይህንን ፋሲካ ከእናንተ ጋር ልበላ እጅግ እመኝ ነበር፤ እላችኂለሁና የእግዚአብሔር መንግሥት እስኪፈጸም ድረስ ወደፊት ከዚህ አልበላም አላቸዉ" (ሉቃስ 22:14-16)፡፡ በቁጥር 7-13 ላይ ጌታችን ጴጥሮስንና ዮሐንስን ልኮላቸው "ሂዱና ፋሲካን እንድንበላ አዘጋጁልን" የሚል ምክር እንደሰጣቸው ተነግሮናል፡፡ ወደ ባለቤቱ ቦታ ሲደርሱ፣ "መምህሩ፡- ፋሲካን ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የምበላበት የእንግዳ ማረፊያ ክፍል የት ነው? ይልሃል" አሉት፡፡

በማቴዎስ 26:26 ላይ "ሲበሉ ሳሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ፤ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ" የሚለውን እናነባለን፡፡ ጌታ እንጀራውን በእጆቹ ይዞ እነዚህን ቃላት ሲናገር በአካል ከእነርሱ ጋር ነበር፡፡ በእጆቹ ያለው የራሱ ሥጋ ሳይሆን፣ ለፋሲካ በተሰጠው ሥርዓት መሠረት የተጋገረና የተዘጋጀ እርሾ የሌለበት እንጀራ ነበር፡፡

የጌታ እራት በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ በሚከበርበት ቦታ ሁሉ እርሾ የሌለበት እንጀራ መጋገር አለበት፡፡ ይህ እንጀራ በጸሎት ይባረካል፡፡ ከዚያም ወደ ብዙ ትናንሽ ቁርስራሾች ተቆርጦ፣ ሁሉም ይካፈላሉ እና የተቆራረሰዉን እንጀራ ይወስዳሉ፡፡ አማኞች እንጀራዉን ሲወስዱ፣ የክርስቶስ ሥጋ ለእነርሱ እንደተደበደበና እንደደቀቀ ያውቃሉ፡፡ ለእነርሱ እንደተሰቀለ ያውቃሉ፡፡ እንዲሁም በፈሰሰው ደም ዋጋ እንደተገዙ ይገነዘባሉ፡፡ አሁን በእግዚአብሔር ባለቤትነት የተያዙና አካሉን የሚሰሩ ናቸው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፦ “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ፤ ጌታ ኢየሱስ ተላልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ፤ ቆርሶም ፦ እንካችሁ ብሉ ፤ ይህ ስለ አናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነዉ. (እባክዎ ‘ስለ እናንተ’ የሚለውን ቃል ልብ ይበሉ)፦ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ ። በተመሳሳይ ሁኔታም ከራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ፤ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና ።” (1 ቆሮ. 11:23-26)።

ጳውሎስ “እኔ ከጌታ ተቀብያለሁ…” ማለት ችሏል። የጌታ እራት እንዴት መከበር እንዳለበት በጌታ በራሱ መመሪያ ተሰጥቶታል። በወንጌላት እንደተጻፈው የጌታ እራትን ሲመሠርት የጌታችንን ቃል ይጠቅሳል።

በሉቃስ 22:20 ላይ እንዲህ ይላል፦ “እንዲሁም ከራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ እንዲህ አለ፦ ይህ ጽዋ ስለእናንተ በሚፈሰዉ ደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነዉ ።” በጽዋው ውስጥ የወይን ጠጅ ነበር። ሊፈስ የነበረው የአዲሱ ኪዳን ደም ገና በደም ሥሩ ውስጥ ነበር እንጂ በመስቀል ላይ አልፈሰሰም። ንጥረ ነገሮቹ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ስለመቀየራቸው ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም። ጌታችንም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ ደም በቀጥታ አልጠጡም። በእርግጥም ጌታችን “የእግዚአብሔር መንግሥት እስከምትመጣ ድረስ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም” የሚል መግለጫ ሰጥቷል። እንጀራና ወይን የክርስቶስን ሥጋና ደም ይወክላሉ፣ ነገር ግን እንጀራና ወይን ሆነው ይቀራሉ። እርሱ ያመለከተው ከሞቱ ቅጽበት በኋላ ወደ ተግባር የሚገባውን አዲስ ቃል ኪዳንና አዲስ ኪዳንን ነው።

ክርስቶስም ቁርባን በሚቀርብበት በእያንዳንዱ ጊዜ ራሱን እንደገና አያቀርብም። እንደ ዕብራውያን 10:12፣ እርሱ ግን ራሱን ስለኃጢት አንድ ጊዜ ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ። በጌታ እራት መካፈል አማኞች በክርስቶስ ሥጋ መስዋዕትነት እና በቅዱስ ደሙ መፍሰስ ምን እንደተፈጸመ በእያንዳንዱ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እንዲገነዘቡ ልዩ ዕድል ይሰጣቸዋል። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ በጌታ እራት ከመካፈሉ በፊት ልቡን መመርመር ይኖርበታል። እግዚአብሔርን የማያስደስት ነገር ባገኘን ቁጥር፣ እንናዘዛለን እና በመሠዊያው ላይ እናስቀምጣለን፣ ደሙ ሁሉንም ነገር ደህና እንዳደረገ በማመን። ለእኛ ሲባል ስለሆነ የጌታችን መከራና በመስቀል ላይ የሞተበት ሥቃይ በውስጣዊ ህመም ይሰማናል ። እንዲህ ያለ ከፍተኛ ዋጋ ለመዋጀታችን በውድ አዳኛችን እንደተከፈለ ስናስብ ትሁት ያደርገናል። በቅዱስ መጻሕፍ መሠረት፣ እርሱ በደሙ ወደ ሰማያዊ መቅደስ ገብቶ በጸጋው ዙፋን ላይ አኖረው፣ በዚህም ዘላለማዊ ቤዛነትን አመጣ (ዕብ. 9:12)።

ደሙ በመስቀል ላይ በፈሰሰበት ቅጽበት ቃል ኪዳን ተደረገ። የድነት ቀን ተጀመረ። ብሉይን ከአዲስ ኪዳን ጋር እንደገና ማነጻጸር አለብን። በዘፀአት 24:6-8 ላይ ስለ ቃል ኪዳኑ መጽሐፍ እና ደግሞ ስለ ቃል ኪዳኑ ደም ተጽፏል፣ በዚህም የቃል ኪዳኑ ሕዝብ ተረጭቷል። ኢየሱስ "ይህ ለብዙዎች ለኃጢአት ስርየት የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነውና" (ማቴ. 26:28) አለ።

በዚህም እርሱ የሚያመለክተው ሊፈስ የነበረውን ንጹሕ፣ ቅዱስና መለኮታዊ ደሙን እንጂ በጽዋው ውስጥ የነበረውን የወይን ጠጅ አይደለም። እርሱ አዲስ ኪዳንን መሰረተ። እኛ የዚያ አዲስ ቃል ኪዳን ሕዝብ ነን እና ወደ አዲሱ የቃል ኪዳን መጽሐፍ ቀጥተኛ መድረሻ እና ግንኙነት አለን።

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለዉ አይደለምን? የምንቆርሰው እንጀራ ከክርስቶስ አካል ጋር ኅብረት ያለዉ አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ አካል ነንና፤ ሁላችንም ከዚያ ከአንድ እንጀራ እንካፈላለንና" (1 ቆሮ. 10:16-17)። እነዚህ ሁለት ቁጥሮች በጣም አልፎ አልፎ ነው ጥቅም ላይ የሚውሉት፣ በእውነቱ ብዙዎች ስለ መኖራቸውም እንኳ ላያውቁ ይችላሉ። ነገር ግን በጌታ እራት ውስጥ የሚገኘውን በጣም ጥልቅ እውነት ይገልጻሉ። ቤተ ክርስቲያንን እንደ አካል፣ በኢየሱስ ስም የሚሰበሰቡ የቅዱሳን ሕያው ኅብረት አድርገው ያሳዩናል። እነርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ፣ አዳኛችን፣ አካሉን ለእኛ የመስዋዕት ሥራ ውጤት ናቸው። በጌታ እራት የምንጠቀመው እንጀራ፣ በአንድ በኩል ስለተሰቀለዉ የክርስቶስ አካል ይናገራል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዚያን የአንድነት አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል፣ ይህም ከብዙ ነጠላ አባላት የተፈጠረ ነው።

የክርስቶስ አካል ተደበደበና ቆሰለ እንጂ አልተሰበረም፣ እንደተጻፈው፦ "ይህ የሆነው የቅዱስ መጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው፦ 'አጥንቱ አይሰበርም'። ደግሞም ሌላ ቅዱስ መጽሐፍ፦ 'የወጉትን ያዩታል' ይላል" (ዮሐንስ 19:36-37)። እዚህ ላይ የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያኑን ምሥጢር እንመለከታለን። በቤዛነት እርሷ የእርሱ አካል ሆናለች — ታርቀውና ተዋጅተው የኃጢአታቸውን ይቅርታ የተቀበሉ ሁሉ ናቸው። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፦ "አካልም አንድ እንደሆነና ብዙ ብልቶች እንዳሉት፣ የአንዱ አካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ቢሆኑም አንድ አካል እንደሆኑ፣ እንዲሁ ክርስቶስም ነውና" (1 ቆሮ. 12:12)። እዚህ ላይ ታላቅ ምሥጢር አለ። ክርስቶስ ከአካሉ አባላት ጋር ብቻ ኅብረት አለው። ስለ እርሱ እንዲህ እናነባለን፦ "እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው" (ቆላ. 1:18)። የእኛ ተፈጥሯዊ አካል አንድ እንደሆነ፣ ነገር ግን በራስ በኩል የሚገናኙና የሚመሩ ብዙ አባላት እንዳሉት፣ እንዲሁ የክርስቶስ አካል አባላት ሁሉ ናቸው። "አይሁድም ብንሆን፤ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ፣ ባሪያም ብንሆን ፤ነጻ ብንሆን ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አንድ አካል ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንድ መንፈስ እንድንጠጣ ተደርገናል።" (1 ቆሮ. 12:13)። ልብ ሊባል የሚገባው፦ በውኃ ሳይሆን፣

እርሱ በመንፈስ በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምኑት እና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በተጠመቁት ሁሉ ውስጥ ይሠራል። ከዚያም እነርሱ በመንፈስ ከክርስቶስ አካል ዉስጥ ይቀመጣሉ። በዚህ መለኮታዊ አንድነት ውስጥ ያሉት የተዋጁ ሁሉ የጌታን አካል ይሠራሉ እና እርሱን እንደ ራስ አድርገው ይገነዘቡታል እና በሁሉም ነገር ለእርሱ ይገዛሉ። ከእያንዳንዱ አባል ጋር ይሰማቸዋል፣ ከሚደሰቱት ጋር ይደሰታሉ፣ ከሚሰቃዩትም ጋር ይሰቃያሉ፣ ምክንያቱም 1 ቆሮንቶስ 12:26 እንዲህ ይላል፡- “አንድም ብልት ቢሰቃይ፣ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ፤ ወይም አንድ ብልት ቢከበር፣ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይደሰታሉ።” በአናንተ ዘንድ እንደዚህ ካልሆነ፣ ከክርስቶስ ጋር ያላችሁን ግንኙነት መርምሩ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በክርስቶስ አካል ዉስጥ የአሉትን አባላት የተለያዩ አገልግሎቶች ልንመለከት አንችልም ። ነገር ግን ጳውሎስ የሚከተለውን መግለጫ ይሰጣል፡- “አሁን ግን እግዚአብሔር እንደወደደ ብልቶችን  ሁሉ በሥጋው ውስጥ እንደ ፈቀደው አስቀምጧል። ሁሉም አንድ ብልት ቢሆኑ ኖሮ አካል ወዴት ነበር? አሁን ግን ብዙ ብልቶች ናቸው፣ ነገር ግን አንድ አካል ናቸው” (1 ቆሮ. 12:18-20) ። በቁጥር 27 ላይ በሚከተሉት ቃላት ጠቅለል አድርጎ ይናገራል፡- “አሁን እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ፣ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።”

ሐዋርያው አማኞች በጌታ እራት ከመካፈላቸው በፊት ልባቸውን እንዲመረምሩ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡- “ሰው ራሱን ይመርምር፣ እንደዚያም ያንን እንጀራ ይብላ፣ ያንን ጽዋም ይጠጣ። የማይገባውም የሚበላና የሚጠጣ፣ የጌታን ሥጋ ሳይለይ በራሱ ላይ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልና” (1 ቆሮ. 11:28-29)። የክርስቶስ አካል የሆኑ ሁሉ እርሱ ፍርዳችንን፣ ኃጢአታችንን — ሁሉንም ነገር በራሱ ላይ እንደወሰደ ያውቃሉ። በዚህ ሙሉ ቤዛነትና ስርየት የሚያምኑም እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላቸው እርስ በእርሳቸው ይቅር ይባባላሉ። ማንም ሰው በሌላ አባል ምንም ነገር አይቆጥርበትም ወይም እርሱን የሚቃወም አይዝም። የጌታን አካል መለየት አለብን። በዚህ ሁኔታ፣ ሙሉ በሙሉ የተዋጁ፣ የጸደቁ፣ የተቀደሱ እና የክርስቶስ ፍጹም፣ እንከን የሌለበትና ያለ እድፍ ወይም መጨማደድ የሆነ  አካል የሆኑትን አባላት ሁሉ ያመለክታል። እርስ በእርሳቸው በክርስቶስና በክርስቶስ በኩል ይተያያሉ፣ እርስ በእርሳቸው እግዚአብሔር እንደሚያያቸው ይተያያሉ፡- ያለ ኃጢአትና ፍጹምነት። እርስ በእርሳቸው በሥጋ አይተዋወቁም፣ ነገር ግን በመንፈስ ነው።

እንጀራዉ ያለ እርሾ እንደሚዘጋጅ፣ ቤተ ክርስቲያንም ከባህላዊ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ ትምህርት አካል ከሆነው ነገር ሁሉ ነጻ መሆን አለበት። ጌታ ኢየሱስ እርሾ የሚለውን ቃል የተጠቀመው በዘመኑ የነበሩ የሃይማኖት መሪዎችን የተሳሳቱ ትምህርቶች ለመጠቆም ነበር። እርሱ፡- “ከፈሪሳዉያንና ከሰዱቃዉያን እርሾ እንድትጠበቁ ብየ ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኩ ለምን አትረዱም? አለ። ያን ጊዜ እንጀራን በሚመለከት

ሳይሆን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት እንዲጠነቀቁ እንዳዘዛቸው ተረዱ" (ማቴ. 16:11-12)።

ጳውሎስም እርሾን ጠቅሶ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ተግብሮታል። በ1ቆሮ. 5:6-8 ላይ እንዲህ ሲል ይጽፋል፡- "ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ አታውቁምን? እንግዲህ እርሾ የሌላችሁ እንደሆናችሁ አዲስ ሊጥ ትሆኑ ዘንድ የድሮውን እርሾ አውጡ። ክርስቶስ ፋሲካችን ነውና እርሱ ስለ እኛ ታርዷልና። እንግዲህ በዓሉን በድሮ እርሾ ወይም በክፋትና በኃጢአት እርሾ ሳይሆን፣ በእውነተኛነትና በእውነት እርሾ የሌለበት እንጀራ እናክብር።" በጌታ እራት የሚካፈል ሁሉ እዚህ ከተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ነጻ መሆኑን በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ይመሰክራል፣ እናም እርሱም በአዲስ ሕይወትና በእውነት የተመሠረተ ነው። ይህ በእውነት መፈጸም አለበት፣ እናም ሕይወቱ የዚያ ምስክርነት ፍሬዎችን ማፍራት አለበት። ቃላት ብቻ በቂ አይሆኑም። እዚያ በትክክ ልምምዱ መኖር አለበት።

በሮሜ 11 ላይ ሐዋርያው የእርሱ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑትን ፍጹም ጽድቅንና መቀደስን ያመለክታል። እነዚህ ነገሮች ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት ተገኝተዋል። ሐዋርያው እንዲህ ሲል ይጽፋል፡- "የመጀመሪያው ፍሬ ቅዱስ ከሆነ፣ ሊጡም ቅዱስ ነውና፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ፣ ቅርንጫፎቹም ቅዱስ ናቸውና" (ቁ. 16)። ክርስቶስ የመጀመሪያው ፍሬ ነው፣ እና ከእርሱ የሆኑት የዚያው አካል ናቸው፤ እርሱ በኩር ነው፣ እና ከተመሳሳይ የእግዚአብሔር ዘር የተወለዱ ሁሉ የበኩር ቡድንን ይሠራሉ። እርሱ የዚህ አዲስ የወይን ግንድ ሥር ነው፣ እና እውነተኛ አማኞች እንደ ዮሐንስ 15 ፍሬ የሚያፈሩ ቅርንጫፎች ናቸው። በተፈጥሮ ውስጥ፣ ቅርንጫፎች ሕይወትን የሚያገኙት ከሥሩ ወደ ወይን ግንዱ በሚመጣው ጭማቂ በኩል ነው፣ ከዚያም የወይኑን ፍሬ ያፈራሉ፣ እንዲሁ በእግዚአብሔር የተወለዱ ሁሉ እንዲሁ ናቸው። እነርሱ ከሆነ ነገር ጋር አይቀላቀሉም፣ ነገር ግን ውጤቱ ናቸው፣ እና በእነርሱ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕይወት ይሸከማሉ፣ ስለዚህም ከመለኮታዊው ባሕርይ ይካፈላሉ። በዚህ ግንኙነት፣ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፡- "በዚህም ላይ ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፤ በበጎነትም እውቀትን፤ በእውቀትም ራስን መግዛትን፤ ራስን በመግዛትም ትዕግሥትን፤ በትዕግሥትም እግዚአብሔርን መምሰልን፤ እግዚአብሔርን በመምሰልም የወንድማማች መዋደድን፤ በወንድማማች መዋደድም ፍቅርን" (2 ጴጥ. 1:5-7)። እዚህ ላይ ትምህርት ወይም ዕውቀት ብቻ አናይም፣ ነገር ግን ይህ መለኮታዊ ውጤትና እውነተኛ አማኝ የሆነው የቤዛነት ሥራ ፍሬ ነው። መስፈሪያው ይህ ነው፡- "ነገር ግን የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ፣ እናንተም በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ 'ቅዱሳን ሁኑ፤ እኔ ቅዱስ ነኝና' ተብሎ ተጽፏልና። ለማንም ሳያዳላ በእያንዳንዱ ሰው ሥራ የሚፈርድ አብን የምትጠሩ ከሆነ፣ የዚህን ዓለም ቆይታችሁን በፍርሃት አሳልፉ" (1 ጴጥ. 1:15-17)።

## ግልጽ ለማድረግ

በመጽሐፍ ቅዱስ ባልተመሰረተ ልማድ ምክንያት ብዙዎች ሁለቱ ንጥረ ነገሮች ወደ ክርስቶስ ደም እና ሥጋ በእውነት እንደሚለወጡ ያምናሉ። ያ በእርግጥ ቢከሰት ኖሮ አስፈሪ በሆነ ነበር። ቅዱስ ሥጋውን በልቶ ቅዱስ ደሙን ጠጥቶ ከዚያም እነዚያ ነገሮች የተፈጥሮ መንገዳቸውን እንደሚሄዱ ማን ሊገምት ይችላል? ይህ አስተሳሰብ ከስድብ አይተናነሰም። ይህ ፈጽሞ የተወገደ ነው።

አይሁዶች የኢየሱስን ቃላት መንፈሳዊ ትርጉማቸዉን ሳይረዱ በተሳሳተ መንገድ እንደተረዱት፣ እንዲሁ የአሁን ከክርስቲያኖች ጋርም ተመሳሳይ ነው። በዚያን ጊዜ ሕዝቡ ጌታችን "ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" (ዮሐንስ 6:54) ሲል፣ ከሕጉ በተቃራኒ እንዲሠሩ እንደጠየቃቸው በማሰብ ዉስጥ ነበሩ። እያንዳንዱ አይሁዳዊ በዘሌዋውያን 17:10-12 ላይ ምን እንደተጻፈ ያውቅ ነበር፡- "ከእስራኤል ቤት ሰው፣ ወይም በእናንተ መካከል ከሚኖሩ እንግዳዎች ማንም ደም የሚበላ ቢኖር፣ ደም በሚበላው ነፍስ ላይ ፊቴን አደርጋለሁ፣ ከሕዝቡም መካከል አጠፋዋለሁ። የሥጋ ሕይወት በደም ውስጥ ነውና፤ ደሙም ለነፍስ ማስተሰሪያ ነውና፣ ለነፍሳችሁ ማስተሰሪያ እንዲሆን በመሠዊያ ላይ ሰጥቻችኋለሁ። ስለዚህ ለእስራኤል ልጆች፡- ከእናንተ ማንም ደም አይብላ፣ በእናንተም መካከል የሚኖር እንግዳ ደም አይብላ ብያለሁ።" በዚህ ምክንያት አይሁዶች ኢየሱስ ሥጋውን ስለመብላትና ደሙን ስለመጠጣት ከተናገረ በኋላ ባደረጉት መንገድ አደረጉ።

ሁለቱ ተፈጥሯዊ ምልክቶች ወደ መንፈሳዊው ይጠቁማሉ። እግዚአብሔር ደምን መጠጣት በእንደዚህ ዓይነት ኃይለኛ መንገድ ከልክሎ፣ ከዚያም ተከታዮቹን እንዲያደርጉት ሊይጠይቅ አይችልም። እንጀራውንና ወይን ጠጁን የሚወስድ ሁሉ በሥጋው መስዋዕትነትና በደሙ መፍሰስ እንደተዋጀ ይመሰክራል። ይህም የዚያ ታላቅ ክስተት መታሰቢያ ነው። ቤዛነትና ስርየት የሚመጣው የጌታን እራት በመካፈል ሳይሆን፣ በጎልጎታ ላይ ተፈጽሟል። በጌታ እራት አማካኝነት በትክክል የተከናወነው ነገር ብቻ ይታሰባል።

በዮሐንስ 6 ላይ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በተመገቡ ጊዜ እንጀራውን በማብዛት የተፈጸመውን ተአምር እናነባለን። በማግስቱ ሰዎች ወደ ጌታ መጥተው እርሱም እንዲህ አላቸው፡- "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁ እና ስለጠገባችሁ ነዉ እንጅ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም።ለሚጠፋ መብል አትስሩ ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕያወት ለሚኖር መብል የሰዉ ልጅ ለሚሰጣችሁ ስሩ ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና " (ዮሐንስ 6:26-27)።

እርሱ ስለ እንጀራ፣ ስለ ምግብ፣ ስለ ዘላለም ሕይወት ተናገረ፣ እናም ሕዝቡ በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ልጆች እንዴት እንደተመገቡ አስታወሱ። ለዚህም ነው "አባቶቻችን

በምድረ በዳ መና በሉ፤ ‘ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው’ ተብሎ ተጽፏልና” (ቁ. 31) ብለው ጮኹ። ኢየሱስም ከዚህ ነጥብ ጋር አገናኘውና “እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ሙሴ ያን እንጀራ ከሰማይ አልሰጣችሁም፤ አባቴ ግን ከሰማይ እውነተኛውን እንጀራ ይሰጣችኋል። የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና። ከዚያም፡- ጌታ ሆይ፣ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ በእኔም የሚያምን ከቶ አይጠማም” (ቁ. 32-35)። ይህ በጣም ግልጽ የሆነ መልስ ነው። የግል ትርጓሜ አያስፈልገዉም። በተመሳሳይ መንገድ በአካል ለመኖር ተፈጥሯዊ እንጀራ እንደምንበላ፣ ለዘላለም ለመኖር ከፈለግን የሕይወት እንጀራ ከሆነው የእርሱ አካል መሆን አለብን።

ጌታ ኢየሱስ ራሱን ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ ለዓለምም የዘላለም እና መለኮታዊ ህይወትን የሚሰጥ አድርጎ ያቀርብልናል ። እርሱ ይህን ሃሳብ በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ያጎላል፡- “እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፣ ሞቱም። ይህ ከሰማይ የወረደ እንጀራ ነው፣ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ማንም ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።” (ቁ. 47-51)

ያ ወንጌል ነው! እርሱ በሥጋው አካል ተሰዋ፣ እኛም ከሥጋችን አካል እንድንዋጅና የዘላለም ሕይወትን እንድንቀበል ነው። ሰማያዊ እንጀራ በምድር አይጋገርም፣ መለኮታዊ ምግብም ከሰው እጅ አይመጣም። ጌታ መስዋዕት ሆነ። የቤዛነት ሥራው ፍጹም እንደሆነ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲቀበሉና በመንፈስ እንዲመገቡ ተሰቀለ። እርሱ የሕይወት እንጀራ ነው። በመንፈስ ከእርሱ ተካፋዮች ነን። እርሱ ከእኛ እንደ አንዱ እንደሆነ፣ እኛም ወደ መንግሥቱ ተመልሰናል የእርሱም አካል ሆነናል።

አይሁዶች እርስ በእርሳቸው ተከራከሩ፡- “ይህ ሰው እንዴት ሥጋውን ሊሰጠን ይችላል?” (ቁ. 52)። ዛሬም ክርስቲያኖች የጌታን እራት በቀላልና በሚያመሰግን ልብ ከመውሰድ ይልቅ ይከራከራሉ። ኃጢአታችንን ያነሳውንና ደሙን ለእኛ ያፈሰሰውን የእግዚአብሔርን በግ እናያለን። ያ ደም ለእኛ ማስተስሪያ ነበር፣ ስለዚህም እርሱ በመሠዊያው ላይ መሰዋት ነበረበት። በክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕይወት ነበረ፣ በሞቱ ደግሞ ያ ሕይወት ነጻ ወጣ እናም ያ ህይወት በእርሱ በተዋጁት ሁሉ ላይ ሊመለስ ችሏል።

የጌታችን ንግግር ወደ መከራውና ወደ ሞቱ ያነጣጠረ ነበር። ለእኛ በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተሰጠንን ከእግዚአብሔር ጋር  መንፈሳዊና መለኮታዊ ህይወት መካፈላችንን መገንዘብ አለብን። በአዲስ ልደት፣ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንሆናለን። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፡- “የአካሉ፣ የአካሉ ብልቶች፣ የአጥንቶቹም አጥንት ነንና” (ኤፌ. 5:30)። በምድራዊ አነጋገር፣ ማንም ከሥጋው ሥጋ ወይም ከአጥንቱ አጥንት የለም። በተፈጥሮ፣ ሁላችንም ከአዳም ነን። በመንፈሳዊ ግን፣

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከሚመነጨዉ የአዲስ ፍጥረት አካል ነን። እንደተዋጁት፣ ወደ እግዚአብሔር ኅብረት ተመልሰናል። በእኛ ነፍሳት ውስጥ የዘላለም ሕይወት የሆነ ሕይወቱ አለን። ሥጋዊ አእምሮ ላላቸው፣ ይህ ሁሉ ሞኝነት ነው፣ ስለዚህም ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሲያነቡ የራሳቸው ሃሳብ አላቸው። መንፈሳዊ ነገሮችን በመንፈሳዊ ነገር መረዳት አለባቸው።

ጌታ ኢየሱስ ብዙ ነገሮች ነው፡- እርሱ መንገድ ነው፣ እውነት ነው፣ ሕይወት ነው፣ ሕያው እንጀራ ነው፣ የዓለም ብርሃን ነው፣ እርሱ ትንሣኤ ነው — እርሱ ለእኛ ሁሉ ነገር ነው። በእርሱ አማካኝነት፣ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሆነን ተመልሰናል። ነገር ግን ኢየሱስ ቃሉን አልብራራም፣ እርሱ ተናገረው ብቻ፤ በዚህ መሠረትም አደረገ፣ እና ከእርሱ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ተፈጸሙ። ስለዚህም “ምግቤ የላከኝን ፈቃድ ማድረግ እና ሥራውን ማጠናቀቅ ነው” (ዮሐንስ 4:34) ማለት ችሏል።

በጌታ እራት የሚካፈል ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በቃሉ እንደተገለጠልን ለማድረግ ከውስጡ ዝግጁ መሆን አለበት። ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። በዚህ መንገድ፣ “ምግቤ የዋጀኝን ፈቃድ ማድረግ ነው” ብለን በእውነት መናገር እንችላለን። የእግዚአብሔርን ቃል እንቀበላለን፣ እናም ከሰማይ የወረደውን ሕያው እንጀራ ክርስቶስን እንቀበላለን። ደሙ ዋጀን፣ ምክንያቱም የፈሰሰዉ ለእኛ ማስተስሪያ ሊሆን ነዉ ።

ኢየሱስ፡- “ይህ ከሰማይ የወረደ እንጀራ ነው፤ አባቶቻችሁ እንደበሉት መና እና በልተው እንደሞቱት አይድለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ግን ለዘላለም ይኖራል” (ዮሐንስ 6:58) አለ። ከዚያ ልዩ ንግግር በኋላ ደቀ መዛሙርቱ፡- “ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነዉ፤ማን ሊሰማው ይችላል?” (ቁ. 60) አሉ። ጌታን የተከተሉት እንኳ ንግግሩን ሲሰሙ የራሳቸው ሃሳብ ነበራቸው። እርሱ ከሰማይ የወረደ እንጀራ እንደሆነ በግልጽ ተናገረ። ነገር ግን ምን ያህል አቅመ ቢስ እንደሆኑ አየ፣ ስለዚህም በቁጥር 63 ላይ፡- “ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም። እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነዉ ሕይወትም ነዉ” አለ። ከላይኛው ብቻ ነው ብርሃንና ጌታ የተናገረው መገለጥ የሚመጣው። ሥጋውን ስለመብላትና ደሙን ስለመጠጣት ያደረገው ንግግር ብዙዎች እርሱን እንዳይከተሉ አደረጋቸው። በዚህ ላይ ክርክሩ እስከ ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። “ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱና ከእርሱ ጋር አልሄዱም” ተብሎ ተጽፏል። ከዚያም ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ፡- “እናንተስ ትሄዳላችሁን?” አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መለሰለት፡- “ጌታ ሆይ፣ ወዴት እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ ፤ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እምነናለ አዉቀናልም ብሎ መለሰለት” (ቁ. 66-69)። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተል ሁሉ ተመሳሳይ ምስክርነት ይኖረዋል። የተናገረውን ቢረዱም ባይረዱም፣

ያምኑታል፣ ያምኑበታል፣ ይታዘዙታል፣ ይከተሉታል፣ ከዚያም ነገሮች ግልጽ የሚሆኑበት ጊዜ ይመጣል።

ስለዚህ ርዕስ ያሉትን ሃሳቦች ጠቅለል አድርገን እንመልከት፦ የቤዛነት ሥራ በጎልጎታ መስቀል ላይ ለአንዴና ለዘላለም ተፈጸመ። በእምነት የሚቀበሉት ሁሉ ያን ታላቅ ቀንና በጎልጎታ የተፈጸመውን ሥራ ለማስታወስ በጌታ እራት ይካፈላሉ። በሚካፈሉት ሰዎች ብዛት መሠረት፣ የዳቦው መጠን ይጋገራል — በእርግጥም፣ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ያለ እርሾ። ከዚያም ዳቦው በጉባኤው ፊት ከፍ ይደረጋል፣ ይጸለይበታል እና በጌታ ስም ይባረካል። ከዚያም ይቆረሳል፣ እና ሁሉም ይካፈላሉና ይበላሉ። የቀረ ነገር ካለ፣ ጥቂት ሰዎች የቀረውን ይበላሉ፣ ስለዚህ ምንም ነገር አይባክንም።

ከዚያም ቀይ የወይን ፍሬ ብቻ መሆን ያለበት ወይን የያዘው ጽዋም በጉባኤው ፊት ከፍ ይደረጋል፣ ይጸለይበታል እና በጌታ ስም ይባረካል። እንጀራውን የበሉ ሁሉ ከዚያም ጽዋውንም ይወስዳሉ። ይህ ሁሉ ጌታችን ሥጋውን እንደሰጠና ደሙን እንዳፈሰሰ ለማስታወስ ይደረጋል።

የጌታ እራት እርሱ ባዘዘው መንገድ መከናወን አለበት። ይህ ካልሆነ፣ እውነተኛው አገልግሎት በፍጥነት ወደ ራስ ጣዖት አምልኮ ይንሸራተታል፣ እና "እምነት" ተብሎ የሚጠራው በእውነቱ ተቃራኒው ይሆናል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፦ "የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ መጠጣት አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ መካፈል አትችሉም። ጌታን ለቅናት እናነሳሳዋለን? ከእርሱስ እንበረታለንን?" (1 ቆሮ. 10:21-22)።

እግዚአብሔር መስዋዕቶች እንዴት እንደሚቀርቡ በተናገረበት በዘሌዋውያን 17 ላይ ያለውን ጥቅስ አስቦ ሊሆን ይችላል። በቁጥር 3-7 ላይ፣ ጌታን የማያስደስቱ መስዋዕቶች ለእርሱ እንዳልተሰጡ በግልጽ ተገልጿል። እንዲህ እናነባለን፦ "...ስለዚህ የእስራኤል ልጆች በሜዳ የሚያርዱትን መስዋዕቶቻቸውን ወደ ጌታ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጅፍ ያመጡታል፣ ወደ ካህኑም አምጥተዉ ለጌታም የደህንነት መስዋዕት ይሰዉት። ካህኑም በመገናኛዉ ድንኳን ደጃፍ ባለዉ በእግዚአብሔር መሰዊያ ላይ ደሙን ይረጨዋል ፤ ስቡንም ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን ያቃጥለዋል ። መሥዋታቸዉንም ደግሞ ተከትለዉ ላመነዘሩባቸዉ ለሰይጣናት አይሰዉ ። ይህ ለእነርሱ ለልጅ ልጃቸዉ ለዘላለም ሥርዓት ይሁን ።"

እግዚአብሔር ትዕዛዙንና ምን እና እንዴት መደረግ እንዳለበት ትክክለኛ መመሪያዎችን ሰጥቷል። እስራኤላውያን ለጌታ እየሠዋን ነው ብለው ያምኑ ነበር፣ ነገር ግን ነገሮችን የራሳቸውን ምናብ ተከትለው ያደርጉ ነበር። ከዚያም እርሱ የአዘዘበት ቦታ ላይ የሚቀርቡት እና እርሱ በሚጠይቀው መንገድ የሚደረጉ መስዋዕቶች ብቻ ከእርሱ ዘንድ እንደሚቆጠሩ በግልጽ አሳወቃቸው። ሌላው ሁሉ ለአጋንንት ይደረግ ነበር።

የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል የሆነ ሁሉ የወደደውን ማድረግ አይችልም። ለእርሱ መደረግ ከአለበት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መደረግ አለበት። ካአለዚያ፣ የራሳችን ምናብ ወደ ምስሉ ከገባ፣ አጋንንት መንገዳቸውን ያገኛሉ። ይህ ለጌታ እራትም እውነት ነው። ጳውሎስ፣ ልዩ ብርሃን ያለው ሐዋርያ እንደመሆኑ መጠን፣ በግልጽ ተናግሮበታል። አማኞች በአጋንንት ተጽዕኖ ሥር ሆነው በጌታ ማዕድ መካፈላቸውን አልፈለገም።

በሐዋርያት ዘመን ስለ ጌታ እራት ክርክር አልነበረም። ጌታ ኢየሱስ ትዕዛዙን ሰጥቶ ነበር፣ እናም አማኞችም ሁሉንም ነገር በቀላሉ ተገበሩ። ለዚህም ነው ቅዱሳት መጻሕፍት እንጀራ በመቁረስ እንደቀጠሉ የሚናገሩት። በሐዋርያት ሥራ 20:7 ላይም "በሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ ለመቁረስ በተሰበሰቡ ጊዜ..." የሚለውን ማንበብ እንችላለን። ከ"እንጀራ መቁረስ" ከሚለው ቃል፣ በጌታ እራት ላይ ትኩረቱ በእንጀራው ላይ እና እንጀራውን በመቁረስ ላይ እንደነበረ እንረዳለን፣ እርሱ ራሱ እንዳደረገው እና ደቀ መዛሙርቱን ተመሳሳይ እንዲያደርጉ እንዳዘዘ። ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ፣ በሐዋርያት ሥራ 2:42 ላይ "በሐዋርያት ትምህርት፣ በኅብረት፣ እንጀራ በመቁረስና በጸሎትም ጸንተው ኖሩ" የሚለውን እናነባለን።

በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ አባል የሆኑ ሁሉ ወደ ተመሳሳይ መጀመሪያው ትምህርትና ልምምድ ይመለሳል። ነገሮችን በትክክለኛ ቦታቸው ያስቀምጣሉ እና በመጻሕፍ ቅዱስ በተገለጸው አሠራር መሠረት ያደርጉታል። ምንም ዓይነት የግል ትርጓሜዎች አይኖሩም፣ ነገር ግን ለቃሉ በቀላሉ መታዘዝ ብቻ ነው። ለእነርሱ ለሚያምኑት፣ ቃሉ የሚለው ብቻ ይገዳቸዋል። ስለዚህም እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን በጎልጎታ የተፈጸመውን ለማስታወስ የጌታን እራት ትካፈላለች። እዚያ ቅዱስ ደሙ ለኃጢአታችን ይቅርታ ፈሰሰ። በመጻሕፍ ቅዱስ ውስጥ ማንም የጌታን እራት የሚካፈል ሰው በዚህ የኃጢአት ይቅርታን እንደሚቀበል የሚገልጽ አንድም ስፍራ የለም። እንደዚህ ተብሎ ትምህርት በሚሰጥበት ቦታ ሁሉ፣ ድነት የሚያርፈው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለው የግል እምነት ላይ ሳይሆን በሃይማኖታዊ ተግባር ላይ ነዉ።

የእግዚአብሔር መንግሥት አሁንም መንገዷን እየያዘች ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፣ የተሰቀለውንና ዳግም የተነሣውና በሁሉ ላይ ጌታ የሆነው፣ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የስብከቱ ማዕከል እየሆነ ነው። እንዲሁም በእዚህ ውስጥ የተሰጠውን እያንዳንዱ ሥርዓት በመታዘዝ መከተልና መጠበቅ አለባቸዉ። በዚህ መንገድ፣ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ጸጋ ወደ መጀመሪያዉ ጅማሬ ትመለሳለች። ጌታችን አልፋ እና ኦሜጋ ነው፣ በእውነትም እርሱ ትናንት እና ዛሬ ለዘላለም ያዉ ነው። እርሱንና ቃሉን ትክክለኛ ቦታ የሚሰጡና እንድናደርግ ያዘዘውን ሁሉ የሚያደርጉ ሁሉ ብፁዓን ናቸው።

# እግር ማጠብ

የጌታ እራትን ካየን በኋላ፣ የእግር ማጠብን ጉዳይ በአጭሩ መንካት አለብን:: በዚህ ሥርዓት ላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለውን ሌላውን ክፍል ከማንበባችን በፊት፣ በብሉይ ኪዳን ካህናት ነገሮችን እንዲያደርጉ እንዴት እንደተሰጡ ማየት አለብን:: ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከመግባታቸው በፊት፣ በመለኮታዊ ሥርዓት መሠረት ለዚሁ ዓላማ የሚሆን መታጠቢያ ነበረ:: መስዋዕት በሚቀርብበት መሠዊያና በድንኳኑ መካከል ተቀምጦ ነበር:: ዘፀአት 30:19ን እናንብብ፡- "...አሮንም ልጆቹም እጃቸውንና እግራቸውን በዚያ ይታጠቡበታል::" እጃቸውንና እግራቸውን አስቀድመው ሳያታጠቡ ወደ ድንኳኑ መግባትም ሆነ ወደ መሠዊያው መቅረብ አይችሉም (ቁ. 20):: በእውነት፣ እግር በሚታጠብበት ጊዜ፣ እጆችም እግረ መንገዳቸዉን ይታጠባሉ:: በአዲስ ኪዳን እውነተኛ አማኞች ቅዱስ ካህናት ተብለው ይጠራሉ :: ወደ እግዚአብሔር መጥተን በታላቅ አክብሮት መቅረብ አለብን፣ ቃሉንም በሁሉም ነገር ማክበር አለብን::

በዮሐንስ 13:4-10 ላይ፣ ጌታችን የሚከተለውን ምሳሌ ሰጠ፡- "ከራት ተነሣ፣ ልብሱንም አኖረ፣ ፎጣንም ወስዶ ታጠቀ:: ከዚያም ውሃውን ወደ መታጠቢያ አፈሰሰ፣ የደቀ መዛሙርቱንንም እግር ማጠብ እና በታጠቀበት ፎጣ ተጠቅሞ እግራቸውን ማበስ ጀመረ:: ከዚያም ወደ ስምዖን ጴጥሮስ መጣ፤ ጴጥሮስም፡- ጌታ ሆይ፣ አንተ እግሬን ታጥባለህን? አለው:: ኢየሱስም መለሰና፡- እኔ የማደርገውን አሁን አታውቀውም፣ በኋላ ግን ታውቀዋለህ አለው:: ጴጥሮስም፡- ከቶ እግሬን አታጥብም አለው:: ኢየሱስም መለሰለት፡- ባላጥብህ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም:: ስምዖን ጴጥሮስም፡- ጌታ ሆይ፣ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጆቼንና ራሴንም ጭምር አለው:: ኢየሱስም አለው፡- የታጠበ ሰው እግሩን ከመታጠብ ሌላ አያስፈልገውም..."

ይህን የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅስ የተከናወነውን ነገር መዘገብ ብቻ እንደሆነ ከተመለከትን፣ እግዚአብሔር ለእኛ እየተናገረ እንደሆነ እንኳን አይሰማንም:: በዚያን ጊዜ ጌታ በዚያ ለነበሩት ተናገረ፣ እና ዛሬም በተመሳሳይ ቃል በተመሳሳይ መንገድ በፊቱ ለመታየት ለሚመጡት ይናገራል:: አሁን ለጥቂት ጊዜ፣ ጴጥሮስ በትክክል በምን እንዳለፈ ማሰብ አለብን:: እርሱ፡- "ጌታ ሆይ፣ አንተ እግሬን ታጥባለህን?" ሲል ጠየቀ:: ጌታም፡- "እኔ የማደርገውን አሁን አታውቀውም፣ በኋላ ግን ታውቀዋለህ" ሲል መለሰ:: ጴጥሮስ

ውሳኔውን አረጋግጦ “ከቶ እግሬን አታጥብም” በማለት ምን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ ፈለገ፡፡ ጌታ በእርሱ ፊት እራሱን እንዲያዋረድና ማንም ቤት ከገባ አገልጋዮች ሊያደርጉት የተገባውን ነገር እያደረገ እንዲታይ አልፈለገም፡፡ ነገር ግን የክብር ጌታና መምህር ለደቀ መዛሙርቱ በጣም ተግባራዊ የሆነ ትምህርት ሰጠ፡- “ከእናንተ መካከል ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋያችሁ ይሁን፡፡” የክብር ጌታ በትህትና አገለገለ፣ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት አሳልፎ በመስጠት፡፡ ልብሱን አውልቆ በምትኩም ቀሚስ ለበሰ፣ ዝቅ ብሎም በቤተሰብ ውስጥ ካሉት ባሪያዎች አንዱ ሆነ፡፡ ይህ ለእያንዳንዱ ሰው ከራሱ ይልቅ ሌላውን ከፍ አድርጎ እንዲመለከት ለደቀ መዛሙርቱ ምሳሌ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ፣ ይህ እንዴት እንደሚደረግ በተግባራዊ ትምህርት አሳይቷል፡፡

ጌታ ጴጥሮስን “ባላጥብህ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም” ሲለው ደነገጠ፣ እና በታላቅ ምኞት የሚከተሉትን ቃላት ብቻ መናገር ቻለ፡- “ጌታ ሆይ፣ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጆቼንና ራሴንም ጭምር፡፡” ይህ ሥርዓትና ትእዛዝ ካልተጠበቀ ከእርሱ ጋር ዕድል እንደሌለው እንዴት ልንረዳ እንችላለን? በእግር መታጠብ ምክንያት ከጌታ ክርስቶስ ጋር ዕድል ያለው ሰው አለን? እዚህ ያለው ነጥብ ጌታ የተናገረውን መታዘዝ ነው፡፡ ይህ ለእርሱም ሆነ እርስ በእርሳችን መፈጸም አለብን፡፡ እርሱ የተናገረው ነገር አስፈላጊ የማይመስል ቢሆንም፣ እርሱ ከተናገረውና ጥያቄ ወይም ሥርዓት ከሆነ፣ ለምን እንደሚሰራ ሳንጠይቅ በቀላል ልጅ መሰል እምነት ማድረግ አለብን፡፡ “ይህን ለምን ማድረግ አለብን?” ብለን መጠየቅ አንችልም፡፡ እርሱ የተናገረውን ካልታዘዝን፣ ከእርሱ ጋር ያለውን ግንኙነት እንቆርጣለን፣ ምክንያቱም እርሱ ሥርዓቱን ሰጥቷልና፡፡ አንድ ሰንሰለት ደካማው አገናኙ እንደሆነው ያህል ብቻ ጠንካራ ነው፡፡ ከእኛ የሚፈለገው በቃልና በሥርዓት መሠረት ማድረግ ነው፣ እርሱንም ለማስደሰት በፈቃደኝነትና በቁም ነገር ማድረግ አለብን፡፡

በዮሐንስ 13:12-17 ላይ የሚከተለውን ጽሑፍ እናነባለን፡- “እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም ወስዶ እንደገና ከተቀመጠ በኋላ፡- ምን እንዳደረግሁላችሁ ታውቃላችሁን? መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ ደግሞም መልካም ትላላችሁ፤ እኔ እንደዚያው ነኝና፡፡ እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ እግራችሁን ካጠብኩ፣ እናንተም እርስ

በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ ያደረግሁትን እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና። እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም፣ የተላከም ከላከው አይበልጥም። እነዚህን ነገሮች ካወቃችሁ፣ ብታደርጓቸው ብፁዓን ናችሁ።"

የመምህሩ ቃላት በጣም ግልጽ ናቸው። እንደተነገሩ የሚወስዳቸዉ ሰው በስህተት ሊረዳቸዉ  አይችልም። እርሱ፡- "እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ እግራችሁን ካጠብኩ፣ እናንተም እርስ በርሳችሁ እግራችሁን መተጣጠብ ይገባችኋል" አለ። ማንም ሰው ማብራራት ወይም የግል ትርጓሜውን መስጠት አያስፈልግም። ጌታ እርስ በእርሳችን እግር መተጣጠብ እንዳለብን ሲናገር፣ የተናገረውን ማለቱ ነው፡- "...እናንተም እርስ በርሳችሁ እግሮቻችሁን መተጣጠብ ይገባችኋል።" ይህ ከምስራቃዊ ወግ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እርሱ በአጠቃላይ ስለሚተገበር ነገር አይናገርም ነበር። እርሱ ይህንን ያውቅ ነበር፣ ነገር ግን በግልጽ እንዲህ አለ፡- "እኔ ያደረግሁትን እንድታደርጉ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።" ይህ ምንም ሊጠየቅ የማይችል ትክክለኛ ሥርዓት ነው። እርሱ ይህንን ትእዛዝ በቃላቱ አጎላ፡- "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም፤ የተላከም ከላከው አይበልጥም።"

ጌታ "እውነት እውነት" ባለ ቁጥር፣ ልዩ ትኩረት ልንሰጥና የተናገረውን በትክክል ልናስተውል ይገባል፣ ምክንያቱም ጠቃሚ ነገርን እያጎላ ነበርና። እዚህ በዮሐንስ 13 ላይ፣ ብዙ ጊዜ አድርጎታል።

ስለ እግር ማጠብ ብዙ ሊባል አይችልም። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ላይ፣ ብዙ ጊዜ ሳይጠቀስ ተረድተዉት እና ተግብረዉታል። ጳውሎስ አንድ ጊዜ የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ሊሰጣቸው ስለሚገቡ መበለቶች ሁኔታዎችን ይጠቅሳል። እናም ይህ በ1 ጢሞቴዎስ 5:10 ላይ እንደሚገኝ እርሱ የሰጠው አንድ ሁኔታ ነበር፡- " ልጆችን በማሳደግ ፣ እንግዳዎችን በመቀበል ፣ የቅዱሳንን እግር በማጠብ፣የተቸገሩትን በመርዳትና ለበጎ ምግባር ሁሉ ራሷን በመስጠት በመልካም ስራም የተመሰከረላት መሆን አለባት።"

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ጌታችን የእግር ማጠብን ሥርዓት እንደመሠረተና ተግባራዊ ምሳሌውን ራሱ እንደሰጠ አሳይተናል። ስለዚህ፣ በእውነት ታማኝ የሆነ ሰው እነዚህን ነገሮች በክርክር ሊያስወግዳቸው አይችልም። መደረግና መታዘዝ አለባቸው። አንድ ሰው አንድን ቅዱስ ጽሑፍ አስረድቶ አድማጮችን ጌታ የሰጠውን ትእዛዝ እንዳይታዘዙ ከመራ፣ ምን እያነሳሳው ነው? ለእያንዳንዱ አማኝ፣ የእግዚአብሔር ቃል ቅዱስ መሆን አለበት፣ እናም ትንሹን ትእዛዝ እንኳን ለመታዘዝና ለመፈጸም ዝግጁ መሆን አለብን። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ የጌታ ቃል ይሠራል፡- "እነዚህን ነገሮች ካወቃችሁ፣ ብታደርጓቸው ብፁዓን ናችሁ።" ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻው ያለው በረከት የሚያርፈው የእግዚአብሔርን ቃል በሚያደርጉት ላይ ነው፣ እና በሚሰሙት ብቻ ግን በማይታዘዙት ላይ አይደለም። ጌታን በእርሱ መንገድ የምንከተልና እርሱ ያዘዘንን የምናደርግ ሕዝብ ያድርገን፣ በዚህ ሁኔታም ቢሆን። ለምን ብለህ አትጠይቅ፣ ሞኝነት ነው አትበል፣ እና አያስፈልግም ብለህ አትመን። ጌታ ተናገረ፣ አዘዘ፣ ተገበረው፣ እናም፡ - "እኔ ያደረግሁትን እርስ በእርሳችሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ" አለ። ይህ በመንፈሳዊው ዓለም "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ማለት ነው። አሜን።

ይኸው ደራሲ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለሚናገሩባቸው በጣም ጠቃሚ ርዕሰ ጉዳዮችን ተመልክቷል ። እነዚህ ብሮሹሮች በዓለም ዙሪያ በብዙ ቋንቋዎች ታትመዋል እና ለብዙ ሰዎች ዘላቂ በረከት ሆነዋል ።

በዚህ የሚሲዮን ማዕከል ውስጥ 21 የተስተካከሉ የዊልያም ብራንሃምን ስብከቶችን አትመናል ፤ እነዚህንም ለሚፈልጉ ሁሉ በጥያቄ ሊላኩ ይችላሉ ። የሚገኙ ህትመቶችን ዝርዝር ማቅረብ ይችላል ።

ውድ ጌታ እና አዳኝ የራሱ ለሆኑት ምን አይነት መንፈሳዊ ምግብ እንዳዘጋጀ ስታውቁ ትገረማላችሁ ።

ፍላጎት ካላችሁ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘረው አድራሻ መጻፍ ትችላላችሁ ፦


ተልዕኮ ማዕከል Mission Center

የፖስታ ሳጥን P.O. Box 100707

47707 Krefeld

Germany

E-mail: volksmission@gmx.de or E.Frank@freie-volksmission.de

Homepage: http://www.freie-volksmission.de